# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 84ኛ ዓመት | ቁጥር 085 | ኅዳር 25 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ለማስተካከል የተጀመሩ ርምጃዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ

ራስወርቅ ሙሉጌታ



ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን መስመር ለማስያዝ የተጀመሩ ርምጃዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) አስታወቁ። የተቀዛቀዘውን የጫት የወጪ ንግድ ለማስተካከልና የንግድ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ገበያዎችን የማስፋት ሥራ እየተከናወነ መሆኑም ገለጹ።

ሚኒስትሩ ትናንት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት ወቅት እንዳስታወቁት ፤ በሀገሪቱ ከፍተኛ የኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አለ። አንዳንድ ነጋዴዎች በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር እያንቀሳቀሱ ለመንግሥት ምንም ግብር አይከፍሉም። በሚያዙበት ወቅት ደግሞ ነገሮችን ፖለቲካዊ ዕይታ በማስያዝ ለማምለጥ ይሞክራሉ።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በሕጋዊ መንገድ እንዲንቀሳቀሱና የግብር ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ እየተሠራ ነው ፤ በመርካቶ የተጀመረውም ይኸው ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ መርካቶ ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አጠቃላይ የንግድ ሥርዓቱ ይዛባል ፤ይህንን ለማስተካከል የተጀመረው ርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የጫት ገቢ ከቡና ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ እንደነበር ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ አሁን ላይ ከዘርፉ የሚጠበቀው ገቢ እየተገኘ እንዳልሆነ አመልክተዋል። አርሶ አደሩ ሆነ ሀገር ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን የፌዴራል መንግሥት ገበያ የማስፋት ሥራዎችን

ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በአማራ ክልል በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልተከናወኑ የሀገራዊ ምክክር ሥራዎች ይከናወናሉ

- በኦሮሚያ ክልል ከታሕሳስ 7 ጀምሮ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ይካሄዳል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡ በአማራ ክልል በቀጣዩ የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልተከናወኑ የሀገራዊ ምክክር ሥራዎች እንደሚከናወኑ ኮሚሽኑ ገለጸ፡፡ በኦሮሚያ ክልል ከታሕሳስ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ እንደሚካሄድም ጠቁሟል፡፡

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ(ፕሮፌሰር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ

በአማራ ክልል በአንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ኢንጂነር ፍቃዱ አለሙ

## ኮርፖሬሽኑ ከ120 ሺህ በላይ ቤቶችን ለመገንባት ማቀዱን አስታወቀ

- ለ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች 336 ሊፍቶች ተገዝተዋል

መክሊት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- በመንግሥት እና የግል አጋርነት ከ120 ሺ በላይ ቤቶችን ለመገንባት ማቀዱን የአዲስ አበባ ቤቶች ኮርፖሬሽን አስታወቀ። ለ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች 336 ሊፍቶች ተገዝተው ሀገር ውስጥ መግባታቸውም ተጠቁሟል።

የኮርፖሬሽኑ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ፍቃዱ አለሙ ፤ ከአዲስ ዘመን

ኮርፖሬሽኑ ከ120 ሺህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የቡና ወጪ ንግድ ፈተናና ውጤት

ምሕረት ሞገስ

ዜና ትንታኔ



በቡና ዘርፍ ከምርት እስከ ዓለም ገበያ ያሉትን ቁልፍ አካላት የያዘ ብሔራዊ የቡና ፕላት ፎርም ሰሞኑን ይፋ ሆኗል። ይህ ፕላት ፎርም በኢትዮጵያ የቡና ወጪ ንግድ ላይ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ተገልጿል። በዚህ ዓመት ከቡና ዘርፍ ብቻ ለማስገባት ከታቀደው ሁለት ቢሊዮን ዶላር እ.አ.አ በ2033 ወደ አራት ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ምቹ መደላድል እንደሚሆን የቡና እና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ በየዓመቱ ወደ ውጭ ትልክ የነበረውን ቡና አስመልክቶ የወጡ መረጃዎች እንደጠቆሙት፤ በ2010 በጀት ዓመት 238 ሺህ 465 ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 838 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል። በ2011 ዓ.ም በ2010 ዓ.ም ከተላከው ያነሰ 230 ሺህ 764 ቶን ቡና በመላክ 763 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ተገኝቷል። አንዴ እየቀነሰ ሌላ ጊዜ ደግሞ እየጨመረ የቀጠለው የቡና የወጪ ንግድ፤ የዘርፉን ችግር ከስሩ በመንቀል ዘላቂ ዕድገት ለማስመዝገብ ከማምረት እስከ ገበያ ድረስ የተሳሰረ የቅንጅት ሥራን የሚጠይቅ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ዘንድሮ ከቡና የወጪ ንግድ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው። በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት አራት ወራት 150 ሺህ ቶን ቡና ወደ ውጪ ተልኳል። ወደ 700 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። ከስድስት ዓመት በፊት ይህ የዓመቱ ገቢ ነበር። ሆኖም ከዚህ በላይ ለማግኘት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው ይላሉ።

እነ ብራዚል እና ኮሎምቢያን የመሳሰሉ ቡና ላኪ ሀገሮች ከሚያመርቱበት ሁኔታ የኢትዮጵያ አመራረት እጅግ የተለየ ነው። በኢትዮጵያ በአንድ ጊዜ በገፍ የሚመረትበት ሁኔታ የለም። የኢትዮጵያ ቡና የሚመረተው በተበታተነ መልኩ ሲሆን፤ አንድ አርሶ አደር ከአንድ ሔክታር በታች ያለው በመሆኑ ወደ ውጪ የሚላከው በብዙ አርሶ አደሮች የተመረተ ቡና ተሰብስቦ ነው። ከዚህ አኳያም ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልከው የቡና ምርት ውስጥ 85 በመቶ የሚሆነው በተበታተነ መልኩ ተመርቶ የተሰባሰበ እንደሆነ ያብራራሉ።

የቡና ወጪ ንግድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ዩኒቨርሲቲው በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ራስ ገዝ ለመሆን ዝግጅት እያደረገ ነው

**ነፃነት አለሙ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ራስ ገዝ ለመሆን አቅዶ የተለያዩ ዝግጅቶችን እያደረገ መሆኑን የዩኒቨርሲቲው ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ችሮታው አየለ (ዶ/ር )ገለፁ።

የዩኒቨርሲቲው ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ችሮታው አየለ (ዶ/ር ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው የረጅም ጊዜ ልምድ ያለውና ትላልቅ ምሁራንን ያፈራ ከመሆኑ አኳያ ራስ ገዝ ለመሆን የሚያስችል አቅም አለው። በአሁኑ ጊዜ ራስ ገዝ መሆን ባይችልም ከሁለት ዓመታት በኋላ ራስ ገዝ ለመሆን አቅዶ ዝግጅት መጀመሩን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ በዋናነት የሰነዶች ዝግጅት ላይ እየሠሩ እንዳሉ የገለፁት ፕሬዚዳንቱ፤ አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲውን ፕሮግራሞች የሚከለሱበት ሰነድ ተዘጋጅቶ በዚህ ሰነድ መሠረት የዩኒቨርሲቲው ፕሮግራሞች ላይ ክለሳ ለማድረግ ሰነዱ ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መቅረቡንና ምላሽ ማግኘቱን ገልፀዋል።

በቀጣይ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት እንዲያየው ፕሮግራም መያዙን ጠቅሰው፤ ሰነዱ ከፀደቀ በኋላ በሰነዱ መነሻነት አጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው ያሉ ኮሌጅና ትምህርት ክፍል ፕሮግራሞች ላይ ክለሳ ተደርጎ ራስ ገዝ ለመሆን በሚያመች መልኩ ፕሮግራሞችን እናደራጃለን ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉንም ፕሮግራሞች ይዞ ላይቀጥል ስለሚችል አግባብነት ያላቸውን ፕሮግራሞች ይዞ ለመሄድ ሰነዱ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው ፤ እስከ ታህሳስ አጋማሽ 2017 ዓ.ም ለሥራ ዝግጁ እንደሚሆን አስረድተዋል።

የራስ ገዝ ማበልፀጊያ ስትራቴጂያዊ እቅድም እየተዘጋጀ መሆኑን አመልክተው፤ እቅዱ እስከ ታህሳስ መጨረሻ 2017 ዓ.ም ድረስ እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ፤ በዕቅዱ ላይም የሚመለከተው አካል ሁሉ አስተያየት ሰጥቶበት፣ ሥራ አመራር ቦርዱ እንዲያውቀው ተደርጎና ተተችቶ ጥር ወር 2017 ዓ.ም በዚህ መነሻነት የምንመራበትን ሰነድ አፅድቀን ሥራ እንጀምራለን ብለዋል።

ከእነዚህ ሥራዎች ባሻገርም አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሕግ ተከልሶ ሙሉ በሙሉ ወደ ማለቁ መድረሱን ጠቁመው፤ በዚህ ሳምንት መጨረሻ ለሴኔት ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ የመጨረሻ ትችት እንደሚቀርብበት ገልፀዋል። ከዚህ በኋላም ወደ ሥራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በቀጣይም ዩኒቨርሲቲው ወደ ራስ ገዝነት የሚሸጋገርበትን ጉዞ በተመለከተ በዝርዝር ተተንትኖና ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ የሚገባበት ሁኔታ እንደሚኖር አስረድተዋል።

እንደ አጠቃላይ በያዝነው 2017 ዓ.ም እነዚህን ሰነዶች የማፀደቅ ሥራ ተሠርቶ በ2018 ዓ.ም ሰነዶቹን ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ እንደሚውሉና 2019 ዓ.ም ላይ ሙሉ በሙሉ ራስ ገዝ ለመሆን በመንግሥት ለማፀደቅና ሥራ ለመጀመር ዝግጁ እንሆናለን የሚል ተስፋ እንዳላቸውም አብራርተዋል።

ዩኒቨርሲቲው ከሃዋሳ ውጪና ሃዋሳ ከተማ ውስጥ ወደ ሰባት የሚሆኑ የተለያዩ ካምፓሶች እንዳሉት ገልፀው፤ ከስፋቱ አንፃር ውጤታማ አድርጎ በልኩ መምራቱ ላይ ተግዳሮት ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል።

በሁለተኛነት ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ግንዛቤ ፈጥሮ አብሮ ለመሄድ በስፋት መሥራት እንዳለባቸው ገልፀው፤ ይህም ሌላኛው ተግዳሮት ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

እነዚህን ዋና ዋና ተግዳሮቶች ለመወጣትም የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ያሳተፈ ሥራ መሥራት አለብን ብለዋል። በተጨማሪም ከአካባቢው መስተዳድር ጋር ተነጋግረውና ራስ ገዝ ለመሆን ያሏቸውን ጉድለቶች መንግሥት አግዞአቸው በተደራጀ ሁኔታ ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚመለከታቸውን አካላት ድጋፍ ለመጠየቅ ማሰባቸውንም አስረድተዋል።



# በክልሉ ከመኸር ሰብል ሰባት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**-ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ተሰብስቧል**

**አመለወርቅ ከበደ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በክልሉ ከመኸር እርሻ ሰባት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ። ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት መሰብሰቡም ተገልጿል።

የክልሉ ምክትል ዕርሰ መስተዳድር እና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ማስረሻ በላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ በመኸር እርሻ ከ345 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በአዝርት እህሎች ተሸፍኗል። ከእዚህም ሰባት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በመኸር እርሻ ከተሸፈነው የአዝርት ሰብል ውስጥ ከ118 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት ላይ የደረሰ ሰብል መሰብሰቡን ጠቁመው፤ በዘመናዊ እና በባህላዊ የምርት መሰብሰቢያ መንገዶች በመታገዝ የደረሰው ሰብል መሰብሰቡን ገልጸዋል።

አቶ ማስረሻ እንደተናገሩት፤ አሁን ላይ በክልሉ የዝናብ ሁኔታው የቀነሰብት ሁኔታ ያለ ቢሆንም፤ ዝናብ በነበረበት ወቅትም የደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳይከሰት ከክልል እስከ ቀበሌ ያሉ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ምርት ለመሰብሰብ ተችሏል።

በክልሉ የመኸር ጊዜ ረዘም ላለ ወራት እንደሚቆይ የገለጹት ኃላፊው ፤ በመኸር እርሻ ከተሸፈነው ሰብል 45 በመቶ ያህሉ የደረሰ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ ከ 118 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የደረሰው ሰብል ነው የተሰበሰበው። ቀጣይ ባሉት ጊዚያት የምርት ማሰባሰብ ሥራው ህብረተሰቡን በማሳተፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

አርሶ አደሩ ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ መጋዘኖችን በማጽዳት ምርት እንዳይበላሽ በማድረግ ምርቱን ከብክነት የመታደግ ሥራዎችን ሊያጠናክር ይገባል ነው ያሉት።

እንደ አጠቃላይ በክልሉ በመኸር እርሻ በአዝርት እህሎች የተሸፈነው መሬት ከእቅድ አንጻር 95 በመቶ ነው። በአትክልትና ፍራፍሬ አንጻርም የማሳ ሽፋኑ ተመሳሳይ ሲሆን፤ በአንድ አንድ ቦታዎች ካልሆነ በስተቀር በሁሉም አካባቢዎች በመኸር እርሻ ለማሳካት የተያዘውን እቅድ ተግባራዊ ሆኗል ሲሉ አስረድተዋል።

ሆርቲካልቸርን በተመለከተም 42 ሺህ 800 ሄክታር መሬት በአትክልትና ፍራፍሬ የተሸፈነ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥም ከ15 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ምርት ተሰብስቧል። በዚህም ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

በመኸር ወቅት በኖራ በታከሙ መሬቶች የአዝርት እህሎችን የመሸፈን ሁኔታ እንደነበር አውስተው፤ በዚህም የተገኘው ውጤት የተሻለ እንደመሆኑ በቀጣይ ትምህርት በመወሰድ ፤ በበልግ ወቅትም መሬትን በኖራ አክሞ የመዝራት ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

አሁን ያለው እርጥበት ለበልግ እርሻ እና ለበጋ ስንዴ ምቹ እንደመሆኑ፤ የመኸር ሰብሉን በማንሳት ወደ በልግ እና ወደ በጋ ስንዴ ምርት ለመግባት እየተሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

## ማህበራት የዋጋ ንረቱን በማረጋጋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

<u>**አዳማ**</u>፡- በመዲናዋ የህብረት ሥራ ማህበራት የዋጋ ንረቱን በማረጋጋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑ የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽን የኢንዱስትሪ ምርት አምራች እና አቅራቢዎች የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበትና ተግዳሮቶቻቸው ላይ የሚወያዩበት መድረክ ትናንት አካሂዷል።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንተባ ዣንጥራራ ዓባይ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ የህብረት ሥራ ማህበራት የህብረተሰቡን ችግር በማቃለልና የሸቀጦች ዋጋ በማረጋጋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛል። ማህበራቱ በከተማዋ በተገነቡ ትልልቅ የገበያ ማዕከላት የተለያዩ ምርቶችና ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እያደረጉ ነው፡፡

የተራዘመውን የግብይት ሰንሰለት ለማሳጠርና ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ለመዘርጋት ማህበራቱን ማጠናከር እንደሚገባ አውስተው፤ ይህም ማህበራቱ በተመጣጠኝ ዋጋ ምርቶችን ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ምቹ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት ከመደበኛው ነጋዴ በዋጋም ሆነ በምርት ጥራት የተሻሉ መሆናቸውን የገለጹት ምክትል ከንቲባው፤ በከተማዋ ባሉ የገበያ ማእከላትም ለእነዚህ ማህበራት ቅድሚያ እንደሚሰጥ ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ባደረገው ሪፎርምም ከዚህ በፊት በህብረት ሥራ ማህበራት ላይ ይነሱ የነበሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መቀነስ መቻሉን አቶ ዣንጥራር ተናግረዋል።

የክልሎች የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርት አቅራቢዎች ከከተማ አስተዳደሩ ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር ተቀራርበው እንዲሠሩም ምክትል ከንቲባው ጥሪ አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ልእልቲ ግደይ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ የግብርና ምርቶችን፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን፣ የእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለከተማው ነዋሪ ለማቅረብ ሸማቹንና አምራቹን በቀጥታ በማስተሳሰር የተረጋጋ ገበያ እንዲኖር ሲሠራ መቆየቱን ገልጸዋል።

የከተማ አስተዳደሩም ኅብረት ሥራ ማህበራት አቅማቸውን ለማጠናከር እና ያጋጠማቸውን የፋይናንስ ዕጥረት ለመፍታት ለዋና ዋና የግብርና እና ለተመረጡ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ማቅረቢያ የሚሆን አንድ ቢሊዮን የተዘዋዋሪ ፈንድ ብር በማመቻቸት ምርቶችን በብዛትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ እንዲችሉ ለአራት ተከታታይ ዓመታት ሳይቋረጥ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል።

ሕገወጥ የምርት አቅራቢዎችን ለመከላከል የህብረት ሥራ ማህበራት ሚና ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት ኮሚሽነሯ፤ ሕገወጥነትን ለመከላከል በህብረት ሥራ ማህበራት መሀከል ቀጣይነት ያለው ትስስር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ወይዘሮ ልእልቲ የምርት አቅርቦት ተደራሽነቱን ይበልጥ ለማስፋፋት የተጀመረው የቅዳሜና እሁድ ገበያ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸው፤ ሕገወጦችን በመከላከልና ማህበረሰቡ ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን ለመቀነስም የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ ተናግረዋል።



# እየተዘነጋ የመጣው የቅድመ ጋብቻ ኤች አይቪ ምርመራ

**ነፃነት አለሙ**

**ዜና ሀተታ**

በኢትዮጵያ ከ600ሺህ በላይ ሰዎች ከኤች አይቪ ቫይረስ ጋር እንደሚኖሩ ከጤና ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያሳያል። በዓመት ከሰባት ሺህ በላይ ሰዎች ለቫይረሱ ተጋላጭ እንደሚሆኑ የጠቆመው መረጃው፤ በየዓመቱ ከ 10 ሺህ በላይ ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ሕይወታቸውን እንደሚያጡ ይገልፃል።

እንደሀገር የስርጭት መጠኑ ከአንድ በመቶ በታች መድረሱ ከወረርሽኝነት መውጣታችንን የሚገልፀው መረጃው፤ በሚፈለገው ልክ ተጋላጭነቱን መቀነስ ያልተቻለው በወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል መሆኑን ያሳያል።

በጤና ሚኒስቴር የኤች አይቪ/ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፍቃዱ ያደታ እንደሚሉት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተለይም ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፍ የኤች አይቪ ቫይረስን ለመከላከል አራት ዋና ዋና እቅዶች ላይ እየሠራ ነው ይላሉ።

የመጀመሪያው ማንኛዋም እድሜዋ ከ15 እስከ 49 የሆነች ሴት ስለ ኤች አይቪ ግንዛቤ እንዲኖራት ማድረግ ፤ ሁለተኛው ደግሞ ከእርግዝና በፊት ራሳቸውን እንዲያውቁ፤ ሶስተኛ ደግሞ ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ከተገኘ ወደ ፅንሱ እንዳይተላለፍ ክትትል ማድረግ እና አራተኛው ከወለዱ በኋላ ለእናትና ለልጁ ምን አይነት ጥንቃቄ መደረግ አለበት የሚል መሆኑን ያስረዳሉ።

ከጋብቻ በፊት መመርመር ዋነኛና ትልቁ ተግባር መሆኑን የጠቆሙት ሥራ አስፈፃሚው ፤አብዛኞቹ እናቶች ኤች አይቪ ፖዘቲቭ መሆናቸውን የሚያውቁት በመጀመሪያ እርግዝና ላይ መሆኑን ይገልፃሉ። የዚህ ዋና ምክንያትም ከጋብቻ በፊት ተመርምሮ አለመጋባት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል ይላሉ።

ይህንንም ለመከላከል ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ላይ በግንዛቤ ማስጨበጫና በባህሪ ለውጥ ዙሪያ መሥራት እንደሚገባ ይገልፃሉ። ኤች አይቪ እንደጠፋ የሚቆጥሩና ከጋብቻ በፊት መመርመር ግዴታ እንዳልሆነ የሚገልፁ መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ግንዛቤውን ተደራሽ ለማድረግ ማህበራዊ ሚዲያዎችን ጨምሮ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። ከዚህ ባሻገር የሃይማኖት ተቋማት ድጋፍም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ምክትል ፕሬዚዳንት የሆኑት መጋቢ ሰንበቱ ባሼ በበኩላቸው በእኛ ስር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ተጋቢዎች ለመጋባት ፍቃድ ሲጠይቁ እስከ ስድስት ወር ድረስ እናቆያቸዋለን ይላሉ። በዚህ ወቅትም ኤች አይቪ ተመርምረው ውጤታቸውን እንዲያመጡ እንደሚደረግ ጠቁመው፤ አሁን ላይ



ሌሎች አጀንዳዎች እየበዙ ከመምጣታቸው አኳያ እንደ ከዚህ በፊቱ በጉዳዩ ላይ ንቃት የመፍጠሩ ነገር ግን በእኛም በኩል ተቀዛቅዟል ሲሉ ያስረዳሉ።

አዲስ ተጋቢዎችን በተመለከተ ግን ጥንቃቄ እናደርጋለን የሚሉት ፕሬዚዳንቱ ፤ በስድስት ወር ቆይታቸው ከሚሰጣቸው ትምህርቶች አንዱ ስለኤች አይቪ መሆኑን ይጠቁማሉ። የእምነቱ አስተምህሮም ግንኙነት የሚፈቀደው በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንደሆነም አንስተዋል። ሌሎች ተቋማትም የእኛን ተሞክሮ ቢወስዱና ቢሠሩበት የስርጭት መጠኑን መቀነስና አስቀድሞ መከላከል ያስችላል ብለዋል።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ሙሉ በሙሉ ቀርቷል በሚያስብል ሁኔታ ወደ ቤተክርስቲያኗ ለመጋባት የሚመጡ ሰዎች የምርመራ ወረቀት ስለመጠየቃቸው ሰምተው እንደማያውቁ የገለፁት፤ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መምህር የሆኑት መጋቢ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ ናቸው።

እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ እንደከዚህ ቀደሙ በቤተክርስቲያኗ አስገዳጅ ተብሎ የኤች አይቪ የምርመራ ወረቀት እየተጠየቀ አይደለም። ይህም እንደሀገር ለበሽታው ከተሰጠው ትኩረት ጋር ተያያዥ እንደሆነ ይገልፃሉ። እንደ ከዚህ ቀደሙ በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በተለያዩ ክበባት በኤች አይ ቪ ዙሪያ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች እንደሌሉ የገለፁት መምህሩ፤ አሁን ላይ ያለው ሁኔታ ግን በሽታው ጨርሶ ጠፍቷል የተባለ ያህል መሆኑን ያስረዳሉ።

የማህበረሰብ ጤናን በተመለከተ የሚካሄዱ ዘመቻዎች የአንድ ሰሞን ብቻ የማድረጉ ነገር ተገቢ እንዳልሆነም ይገልፃሉ። መንግሥትም ሆነ ሃይማኖት ሕዝብ ሲኖር ነውና የሚኖሩት ኤች አይ ቪ ላይ ብቻ ሳይሆን አሁን እየተስፋፉ የመጡትን ተላላፊ ያልሆኑ እንደልብ፣ ካንሰር፣ ስኳርና ደምግፊት የመሳሰሉ በሽታዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ ቢሠራ የሚል መልዕክታቸውንም አስተላልፈዋል።

# "ብሄራዊ ጥቅምን በሚያስከብሩ ጉዳዮቻችን ላይ የጋራ አቋም መያዝ አለብን"

- ኡስታዝ ጀማል በሽር

**ሰሚራ በርሀ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን በውስጥ ግጭቶች እና ልዩነቶችን ከሚፈጥሩ አጀንዳዎች ይልቅ ብሄራዊ ጥቅምን በሚያስከብሩ አጀንዳዎች ላይ የጋራ አቋም መያዝ አለብን ሲሉ ኡስታዝ ጀማል በሽር ገለጹ፡፡

ኢትዮጵያ የዓባይ ጉዳይን በተመለከተ ያላትን አቋም ለአረብ ሀገራት በአረብኛ ቋንቋ በስፋት በማድረስ የሚታወቁት ኡስታዝ ጀማል በሽር እንደ ሕዝብ ብሄራዊ የሆኑ አጀንዳዎቻችን ላይ አንድ ሆነን መቆም አለብን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኡስታዝ ጀማል ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ግብጻውያን በመሀከላቸው መከፋፈል ቢኖርም በሀገር ጉዳይ ላይ ያላቸው አንድነት ጠንካራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ግብጻውያን በየትኛውም የሥራ ዘርፍ ላይ የሚገኙ ፤ ረጅም ዓመት ተፈርዶባቸው በእስር የሚገኙ ዜጎቻቸው ጭምር በሀገራቸው ጉዳይ ያላቸው አቋም አንድ ከመሆኑም በላይ ጠንካራ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የዓባይ ውሃ ባለቤት ብትሆንም በዜጎች ዘንድ የሚሰጠው ትኩረት ሊሠራበት የሚገባው መሆኑንም አንስተዋል፡፡ እንደሀገር በትምህርት ሥርዓታችን ውስጥ ተተኪ ለሆኑ ትውልዶች ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብትና የዓባይን ውሃ የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሠጥቶ በመሥራት ላይ ያለን ተሞክሮ ደካማ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጉዳይ ሊሻሻል የሚገባ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከዚህ ቀደም የነበሩ መሪዎች ዘንድ በእቅድ ላይ የነበረ መሆኑን ያስታወሱት ኡስታዝ፤ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ሥራ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ አሁን ላይም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ጠንካራ ሥራዎች መሠራታቸውን አንስተዋል፡፡

ኡስታዝ ጀማል ሀገርን ወክለው በዓባይ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያ ያላትን አቋም በማሳወቅ በበርካታ የመገናኛ ብዙሃን ላይ በመቅረብ እና የራሳቸውንም ሚዲያ በማቋቋም በአረብኛ ቋንቋ በአረብ ሀገራት መገናኛ ብዙሃን ላይ በመሞገት ይታወቃሉ ፡፡



# 2ኛውን ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ የጋራ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል


**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሁለተኛውን ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የጋራ ርብርብ ማድረግ እንደሚገባቸው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከንቲባ አዳነች የሁለተኛውን ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ አፈጻጸም አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት፣ ከሥራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች ጋር ትናንት ተወያይተዋል።

ይህን አስመልክተው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት እንደገለጹት፤ በመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ በጥራትና በፍጥነት ስኬታማ ሆኖ ተጠናቋል። ከእዚህ የተገኙ ልምዶችን በመቀመር የተጀመረውን ሁለተኛ ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ በተያዘለት ጊዜና ጥራት በማጠናቀቅ ለነዋሪዎች አገልግሎት ክፍት ማድረግ ይገባል።

የሁለተኛው ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ ከመጀመሪያው ዙር አንጻር ሰፊና የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸው፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘላቂ ልማትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በትብብር፣ በተያዘለት ጊዜ፣ በጥራት ደረጃውን (ስታንዳርዱን) ጠብቀው እንዲያጠናቅቁ የጋራ መግባባት ላይ መደረሱን አመልክተዋል።



ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

በትራፊክ መጨናነቅና አንዳንድ ምቾት በማይሰጡ ጊዜያዊ ሁኔታዎች ለተንገላታችሁ የከተማችን ነዋሪዎች ይቅርታ እጠይቃለሁ ያሉት ከንቲባዋ፣ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በውጤቱ እንደምንክሳችሁ ቃል ለመግባት እወዳለሁ ብለዋል።

# በአማራ ክልል በአንድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል በወረዳ ደረጃ ተሳታፊዎችን የሚያስመርጡ ከሁለት ሺህ 200 በላይ ተባባሪዎች ሥልጠና ተጠናቋል፡፡

በክልሉ በብዙ ወረዳዎች ተባባሪ አካላት ተሳታፊዎችን በመለየት አስመርጠዋል ያሉት ዋና ኮሚሽነር ፤ በቀጣዩ የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀሪ የምክክር ሥራዎችን ለማካሄድ መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ አሁን ላይ የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ለዋናው የሀገራዊ ምክክር ጉባዔ የሚሳተፉ ተወካዮችን የማስመረጥ ሂደት ላይ መሆኑን ያመላከቱት ዋና ኮሚሽነሩ፤ ሥራው በ9 ክልሎች እና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች መጠናቀቁን አውስተዋል፡፡

ከታሕሳስ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የኦሮሚያ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ለዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባዔ ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ እንደሚከናወንም ጠቁመዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ከ350 በላይ ወረዳዎች ከሚመጡ ከሰባት ሺህ 700 በላይ ተሳታፊዎች እና ከክልሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የክልሉን አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራ እንደሚከናወንም ተናግረዋል፡፡

እንደ መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር) ገለጻ፤ ቀሪ ዓበይት ሥራዎች የፌዴራል ባለድርሻ አካላትን በመሰብሰብ አጀንዳ እንዲሰጡ ማድረግ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚኖሩ የዲያስፖራ ማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በመገናኘት አጀንዳቸውን እንዲልኩ እና በሚሰጣቸው ቀመር መሠረት ተሳታፊዎችን እንዲልኩ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ሥራውን 80 በመቶ የተሟላ እንደሚያደርገው ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ ትግራይ ክልል በመሄድ አንዳንድ ባለድርሻ አካላትን ማነጋገሩን አስታውሰው፤ በክልሉ በኩል ፍላጎት መኖሩን ገልጸዋል፡፡ በትግራይ ክልል ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ጋርም ጥሩ የሚባል ውይይት መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

አሁን ላይ ኮሚሽኑ ከክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር፣ በክልሉ ካሉ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች ጋር ለመነጋገር በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጸው ፤ በክልሉም በኩል ምላሹ መልካም መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በትጥቅ ትግል ላይ ላሉ እና ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር አብረው መሥራት ላልጀመሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኮሚሽኑ በተደጋጋሚ ጥሪ እንደሚያደርግ የገለጹት ዋና ኮሚሽነሩ፤ አንዳንዶቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅድመ ሁኔታ እንደሚያስቀምጡ እንዲሁም አንዳንዶቹ ደግሞ በኮሚሽኑ ላይ ጥርጣሬ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

ምክንያቱ አሳማኝ አይደለም የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ ኮሚሽኑ አሁን ላይ ከ50 በላይ ከሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እየሠራ እና የሚሠራውን ሥራ ፓርቲዎቹ እየተመለከቱ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ኮሚሽኑ ሁሉንም ማሳተፍ ስላለበት በትጥቅ ትግል ላይ ካሉ አካላት ጋር ቅርበት ሊኖራቸው ከሚችል የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ አካላት ጋር በተቻለ መጠን አሁንም ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረው፤ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ሁሉም በሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ኮርፖሬሽኑ ከ120 ሺህ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተጠየቅ አምድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት ፤ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት እና የግል አጋርነት ከ120 ሺህ በላይ ቤቶችን ለመገንባት አቅዷል። ከዚህ ውስጥ 60ሺ ቤቶች የሚገነቡት በአቪድ ሪል እስቴት ነው።

ለውጡ ሲጀመር ኮርፖሬሽኑ 54 ቢሊዮን ብር እዳ እንደነበረበት ፤ የተለያዩ አሠራሮችን በመተግበር እዳውን ወደ 32 ቢሊዮን ብር መቀነስ እንደቻለ የጠቀሱት ኢንጂነር ፍቃዱ፤ አሁን ላይ ለእዳው በቀን ስምንት ሚሊዮን ብር ወለድ እየተከፈለ እንደሆነ አስታውቀዋል። እዳውን ባለመክፈሉም ለግንባታ የሚሆን አዲስ በጀት ማግኘት እንዳልተቻለ አመልክተዋል።

ኮርፖሬሽኑ አዳዲስ ግንባታዎችን ለመጀመር በመቸገሩ በከተማ አስተዳደሩ በተጠና ጥናት ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ጀምሯል ያሉት ኢንጅነሩ ፤ ከዚህ ውስጥ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስትራቴጂ አንደኛው ነው። በዚህም ከ22 አልሚዎች ጋር የመንግሥት እና የግል አጋርነት ውል ተፈራርመናል። ሰባቱ አልሚዎችም ወደ ሥራ ገብተው ግንባታ ጀምረዋል ብለዋል።

ከአሳንሰር (ሊፍት) ጋር በተያያዘም ለሚነሱ ቅሬታዎች፤ አሁን ላይ በጣም ብዙ ህንፃዎች አሳንሰር /ሊፍት/ ያስፈልጋቸዋል። ከዶላር ጭማሪው ጋር ተያይዞ አንድ ሊፍት ከዚህ ቀደም ከነበረው ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ጭማሪ ማሳየቱን አመልክተዋል።

የሊፍት ገጠማ ሥራው ከፍተኛ ገንዘብን ይጠይቃል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ፤ ይህም ሆኖ የነዋሪዎችን ችግር ለመቅረፍ አሁን ላይ የተወሰኑ ሊፍቶችን ለመግዛት ጨረታ አውጥተን በሂደት ላይ እንገኛለን ብለዋል።

ከእነዚህ ውስጥ ለ40/60 ፕሮጀክቶች የሚሆኑ 336 ሊፍቶች ግዥ ተፈጽሞ ሀገር ውስጥ ገብተዋል።70 የሚሆኑ ሊፍቶች የመገጣጠም ሥራ ተጀምሯል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ፤ ከሊፍት ከአቅራቢው ጋር የተወሰነ ችግር አጋጥሞ እንደነበር እና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በጋራ በመሆን ችግሩን መፍታት እንደተቻለም ጠቁመዋል።

ለ20/80 ፕሮጀክቶች ሊፍት ለማቅረብ አራት ድርጅቶች ጨረታ ማሸነፋቸውን ፤ ከእነዚህ መካከል አሁን ላይ ሥራቸውን በአግባቡ እየሠሩ ያሉት ሁለቱ መሆናቸውን አመልክተዋል። ከሁለቱ አንደኛው የሊፍት ገጠማ ሥራውን ማገባደዱን አስታውቀዋል። በጨረታ ካሸነፋቸው ህንፃዎች ሁለት ብቻ እንደቀሩትም ገልጸዋል።

የሊፍት ገጠማ ሥራው እየተከናወነ ያለው ለአሁኖቹ ግንባታዎች ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ለተገነቡ ህንጻዎች ጭምር ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ፤ አሁን ላይ በነባር ፕሮጀክቶች ላይ የነበረው የሊፍት ገጠማ ችግር በአብዛኛው እየቀረፈ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሁለተኛው የሊፍት አቅራቢ ድርጅት ማቅረብ ከነበረበት 230 በላይ ሊፍቶች ግማሽ ያህሉን አቅርቧል። ከ120 በላይ ለሚሆኑ ህንጻዎች የገጠማ ሥራዎችን ሠርቷል። ቀሪ ሥራዎችን በፍጥነት እንዲያጠናቅቅ እየተነጋገርን ነው ብለዋል።

ጨረታ ያሸነፉ ሌሎች ሁለት ድርጅቶች በሥራ ላይ እንደሌሉ አመልክተው ፤ ለበሻሌ ሳይት አሳንሰር ለማቅረብ የተዋዋለው ድርጅት በውሉ መሠረት ሥራዎችን እያከናወነ ባለመሆኑ ውሉ ተቋርጧል። ይህን ተከትሎም በሻሌ ሳይት አዲስ ጨረታ ለማውጣት በሂደት ላይ እንደሆነ አስታውቀዋል።

በዚህ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ያደረግነውን ሙሉ ቃለምልልስ በተጠየቅ ዓምዳችን ላይ ያገኙታል።

# ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እያከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

በመንግሥት በኩል የጫት ኬላዎች እንዲነሱ ቢወሰንም የተለያዩ ሰበቦች እየተፈለጉ 283 ሕገ ወጥ ኬላዎች በመላው ሀገሪቱ አሉ ያሉት ሚኒስትሩ ፤ እነዚህ ኬላዎች የምርት ነጻ ዝወውርን የሚገድቡ፤ የሎጀስቲክ መቀላጠፍን የሚያደናቅፉ፤ በአጠቃላይ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥሩ በመሆናቸው የሚመለከታቸው አካላት ርምጃ እንዲወስዱ ማሳወቃቸውን ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት በጫት የወጪ ንግድ አራት ሺ 900 ነጋዴዎች ፈቃድ አውጥተው የነበረ ቢሆንም የሚልኩት ከ300 ያልበለጡ ነበሩ ያሉት ሚኒስትሩ ፤ ብዙዎቹ ፈቃዳቸውን የሚጠቀሙበት ለኮንትሮባንድ ማስተላለፊያነት ነበር። ይህንንም ለመቅረፍ የንግድ ፈቃድ ቅድመ ብቃትን ያረጋገጠ መሆን አለበት ተብሎ ባለፈው ዓመት 347 ፈቃድ አውጥተው እንዲሠሩ ተደርጓል ብለዋል ።

አሁን ላይ ስድስት መቶ የሚደርሱ ነጋዴዎች በሥራ ላይ ይገኛሉ። ይህንን ለማስቀጠል የንግድ ፈቃድ እድሳት መመሪያው ለእድሳት የአንድ ወር ጊዜ ቢያስቀምጥም ዘንድሮ ከሀምሌ ጀምሮ እስከ ህዳር ሰላሳ 2017ዓ.ም ድረስ እየተከናወነ ይገኛል። የኮታ አሠራር መቆሙ ለጫት የወጪ ንግድ ተጨማሪ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩንም ጠቁመዋል።

የሰንበት ገበያን በተመለከተ ሚኒስትሩ በሰጡት ማብራሪያም ፤ በሩብ ዓመቱ 59 የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች እንዲመሠረቱ ተደርጓል ፤ እንደ ሀገር የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች አንድ ሺህ 134 እንዲደርሱ ተደርጓል። እነዚህ ገበያዎች ከአስር እስከ ሰላሳ በመቶ የዋጋ ቅናሽ ያለባቸው ናቸው። የጥራት ጉድለት ላለባቸው ገበያዎችም ደረጃ በማዘጋጀት ነባር ገበያዎች ወደ ተዘጋጀው ደረጃ እንዲያድጉ፤ አዳዲስ ገበያዎች በደረጃው መሠረት እንዲገነቡ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

አንዳንድ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተነሳሽነት ወስደው እየሠሩ ይገኛል ፤ አዲስ አበባ መስተዳድር በቢሊዮን የሚቆጠር ብር በመመደብ በለሚኩራ እና በኮልፌ የግብርና ምርት ማቅረቢያ ማእከላት ገንብቷል። አማራ ክልልም 450 ሚሊዮን ብር በመመደብ የአንደኛ ደረጃ የግብይት ማእከላትን በመገንባት ላይ ይገኛል። እነዚህ ማእከላት ከደላላ ውጪ ግብይት እንዲፈጸም የሚያስችሉ ፤ ጤናማ የንግድ ሥርዓት እንዲኖር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ብለዋል።

ሚኒስትሩ ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ ለአንድ ቀን በተደረገ አሰሳ ካሉት 120 ማደያዎች አገልግሎት ሲሰጡ የነበረው ስድስት ብቻ ሲሆኑ ስልሳ ስምንቱ ነዳጅ እያላቸው የለም ሲሉ መገኘታቸውን አስታውቀዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከተጀመረበት ቀን አንስቶ እስካሁን ድረስ በየቀኑ ላለፉት 125 ቀናት የገበያ ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፤ በዚህም በመላው ሀገሪቱ ከ105 ሺህ በላይ ነጋዴዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል። ከዚህ ወስጥም ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑት በእስራት እንዲቀጡ መደረጉን አንስተዋል ።

# የቡና ወጪ ንግድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደ አዱኛ (ዶ/ር) ገለፃ፤ በኢትዮጵያ እንደሌሎቹ ሀገሮች ከቡና ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ብዙ ሥራን ይጠይቃል። የተበታተነውን የመሰብሰብ ችግር እንዳለ ሆኖ ጉዳቱን ለመቀነስ፤ ቡና ገዝተው የሚልኩ ቡና ላኪዎች ጥራት ያለው የቡና ምርት ለዓለም ገበያ በማቅረብ ተወዳዳሪ ሆነው ለመገኘት ከአርሶ አደሩ ጋር ይሠራሉ። ሆኖም አሁንም የኢትዮጵያ ቡና በጥራት ተወዳዳሪ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል።

አዱኛ (ዶ/ር) እንደሚያብራሩት፤ ቀደም ሲል ቡና የፖለቲካ ጉዳይ ነው በሚል በውጪ ፕሮጀክት አይደገፍም ነበር። አሁን ግን ካለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ ዘርፉን ነፃ በማድረግ ቡና ላይ ፕሮጀክቶች እንዲመጡ እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ ሰፊ ዕድል ተፈጥሯል። ሆኖም በየዓመቱ ትልቅ ገቢ ለማግኘት አልተቻለም ነበር። የዚህ ምክንያት ፕሮጀክቶች ቢኖሩም እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል የሚንቀሳቀሰው በራሱ ነው።

ብሔራዊ የቡና ፕላት ፎርም መፈጠሩ ማንኛውንም ከቡና ጋር በተያያዘ የሚሠራ የፕሮጀክት ሥራ በተበታተነ መልኩ ከመሥራት ይልቅ፤ ሰብሰብ ተብሎ በጋራ ለመጓዝ ያግዛል። ማን ምን ይሠራል? ምን ያህል ገንዘብ አለው? የትኛው ወረዳ ላይ የትኛው ቦታ ላይ ይሠራል? የሚለውን በመለየት ድግግሞሽን ለመቀነስ ይረዳል ነው ያሉት።

ሰብሰብ ብሎ መሥራት ምርትና ምርታማነትን ከመጨመር፤ ጥራትን ከመጠበቅ፣ ገበያን ከማፈላለግ እንዲሁም ኢትዮጵያ 30 በመቶ የቡና ምርት ወደ አውሮፓ የምትልክበት ሁኔታ ላይ የተጋረጠውን አደጋ ማለትም አዲሱን የአውሮፓ ሕብረት የአካባቢ ጥበቃ ሕግ መስፈርትን ማሟላት እንዲቻል ከማገዝ አንፃር ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ነው የተናገሩት።


95 በመቶ የሚሆነው ቡና በማህበሩ በኩል ለውጭ ገበያ እንደሚላክ የሚናገሩት፤ ደግሞ የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ደሳለኝ ዜና ፤ ማህበሩ በ15 ዩኒየኖች አማካኝነት ከሶስት ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮችን ያቀፈ ሲሆን፤ በተለይ ከፍተኛ ቡና አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች በዋናነት በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልሎች ያሉትን ሁሉ ያካተተ መሆኑን ተናግረዋል።

ምርቶቹ የሚመረቱት ራቅ ባሉ አካባቢዎች መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ መሆኑ ደግሞ ቡና ከሚመረትባቸው አካባቢዎች ወደ ማዕከል ለማምጣት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ተናግረዋል። ቡናን ሰብስቦ ወደ ማዕከልም ሆነ ወደ ጂቡቲ ለመላክ የተለያዩ ውጣ ውረዶች ያጋጥማሉ። በዋናነት የሎጅስቲክ ችግር እየፈተናቸው መሆኑን አስረድተዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም በኢትዮጵያ ባቡር ድርጅት በኩል ለመላክ፤ አዲስ አበባ ሆኖ በኮንቴነር ለማሸግ ኮንቴነር ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተፈለገው ጊዜ በባቡርም ሆነ በመርከብ በዓለም ገበያ ላይ ለማድረስ የቡና እና ሻይ ባለሥልጣን እና ሌሎቹም ጥረት በማድረጋቸው፤ ብዙ ችግሮችን ተቋቁመው ሥራዎች በመሥራታቸው አሁን የተገኘውን ውጤት ማግኘት ተችሏል ነው ያሉት።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልከው ውስጥ ከ30 በመቶ በላይ የሚሆነው ቡና የሚላከው ወደ አውሮፓ ነው። አሁን ደግሞ አውሮፓ ህብረት (ዩኒየን) ያወጣው የአካባቢ ጥበቃ ሕግ ለአርሶ አደሩም ሆነ ለቡና ላኪዎች ፈተና ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ይገልጻሉ።



ባለፈው ዓመት ከቡና ወጪ ንግድ አንድ ነጥብ 43 ቢሊዮን ዶላር የተገኘው በከፍተኛ ጥረት መሆኑን የሚናገሩት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡና ማህበር ፕሬዚዳንት ሁሴን አምቦ (ዶ/ር)፤ ጥራት ያለው ቡና በማምረት፣ በማጓጓዝ እና የተገባውን ቃል በመፈፀም በአጠቃላይ መንግሥት እና የግል ዘርፉ ተዋናዮች ከፍተኛ ጥረት በማድረጋቸው ውጤት መገኘት መቻሉን ገልፀዋል።

የኤግዚቢሽን ደረጃዎችን በማሳደግ ጅማ፣ ሃዋሳ እና ድሬዳዋ ላይ የውጭ አገር ገዢ እና የሀገር ውስጥ አምራቾችን በማሳተፍ መሃል ላይ ያለውን ሰንሰለት በመቀነስ በተሠራው ሥራ መፍትሔዎች ተገኝተዋል ነው ያሉት።

እንደ ሁሴን (ዶ/ር) ገለፃ፤ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በዓለም ባለልዩ ጣዓም ቡና ተወዳድረው አንድ ኪሎ ቡና 104 ሺህ ብር ተሸጧል። ጥራቱ እየጨመረ አርሶ አደሩ ለጥራቱ ተገቢውን ዋጋ እያገኘ ነው። ነገር ግን አምራቹ ገበሬ በቀጥታ ከውጭ ገዢው ጋር የማገናኘት ሥራ መሠራት እና ይህንን እንቅስቃሴም ማስቀጠል እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

የኢትዮጵያ ቡናን ወደ ውጭ የመላክ ጉዞ በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ ያለፈ ቢሆንም፤ አሁን ላይ አርሶ አደሩ ለጥራት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ፤ የዘርፉ ተዋናዮች ሥራ የተደራረበ እንዳይሆን እና ተናበውና ተቀናጅተው እንዲሠሩ ብሔራዊ ፕላትፎርም በመፈጠሩ፣ እንዲሁም ግልፅ ፍኖተ ካርታ በመዘጋጀቱ በቀጣይ በዓለም ተወዳዳሪ መሆን እንደሚቻል አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት የአቪዬሽን ዘርፉ ሚና የማይተካ ነው!

ጠንካራ ተቋማት የጠንካራ ሀገር መሠረቶች ናቸው፡፡ የጠንካራ ተቋማት ባለቤት የሆኑ ሀገራት ጽኑ መሠረት ያላቸው በመሆኑ ሀገርን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያሸጋግራሉ፤ የሀገርን ገጽታ ይገነባሉ፤ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖም ይፈጥራሉ፤ ቋሚ አምባሳደር ሆነውም ሀገርን ያስተዋውቃሉ፡፡ በአጠቃላይ የሀገር መለያ ሰንደቅ ዓላማ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

ይህንኑ በመረዳት ኢትዮጵያም ዘላቂ እና ጠንካራ የሆኑ ተቋማትን ለመገንባት ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ መንግሥት በተቀያየረ ቁጥር የማይቀያየሩ፤ ዘላቂነት ያላቸውና በየትኛውም ጊዜና ቦታ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርገው የሚያስተዋውቁ ተቋማትን ለመፍጠር ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡ በዚህ ረገድም ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ያገኙ ተቋማት ከመኖራቸውም በሻገር ከወዲሁም የብዙዎችን ቀልብ መሳብ የቻሉና ከኢትዮጵያም አልፈው አፍሪካን ማኩራት የሚችሉ ተቋማትም እየተፈጠሩ ነው፡፡

ዓለምአቀፍ እውቅናን ካገኙና ከኢትዮጵያ አልፈው የአፍሪካ ኩራት ከሆኑ ተቋማት ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መንግሥታት በተቀያየሩ ቁጥር የማይዋዥቅና ጥንካሬውንም አስጠብቆ ከዘመን ወደ ዘመን መሸጋገር የቻለ የጠንካራ ተቋማት ምሳሌ ነው፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በኢንዱስትሪው የአቪዬሽን ኦስካር ተብሎ በሚጠራው የስካይትራክስ መድረክ ለሰባተኛ ጊዜ የአፍሪካ ምርጡ አየር መንገድ ሽልማትን አሸንፏል፡፡ አየር መንገዱ በተጨማሪም የአፍሪካ ምርጥ የቢዝነስ ክፍል አየር መንገድ ሽልማትን ለ6 ተከታታይ ዓመታት ማሸነፍ ችሏል፡፡

እንዲሁም አየር መንገዱ የአፍሪካ ምርጥ የኢኮኖሚ ክፍል አየር መንገድ ሽልማትን ለ6 ተከታታይ ዓመት ለማሸነፍ በቅቷል፡፡ ከዚህ ባለፈም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ክፍል ምርጥ ምግብ አገልግሎት ሰጪ አየር መንገድ ሽልማትን አሸንፏል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ አየር መንገዶችን ብቃት የሚገመግመው ስካይትራክስ ድርጅት የኢትዮጵያ አየር መንገድን የ2024 ምርጡ የአፍሪካ አየር መንገድ በሚል ሰይሞታል፡፡ ይህንንም ሽልማት ለተከታታይ ሰባት ዓመታት ማግኘት ችሏል፡፡ አየር መንገዱ የአፍሪካ ምርጥ ቢዝነስ ክላስና ኢኮኖሚክ ክላስ እንዲሁም በአፍሪካ ለኢኮኖሚ ክላስ ተጓዦች ምርጥ የበረራ ላይ ምግብና መጠጥ አቅራቢነት በጥቅሉ አራት ሽልማቶችን አግኝቷል።

ወደ ስምንት አስርት ዓመታት የሚጠጋ እድሜ ያስቆጠረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይህ ሁሉ ስኬት ማሳካት የቻለው የአየር መንገዱ አመራሮች እና ሠራተኞች ከሚያደርጉት ያላሰላሰ ጥረት እና ከመግሥት ትኩረት ባሻገር የጀርባ አጥንት ሆኖ ለስኬቱ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ያለው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን ነው፡፡

እ.ኤ.አ. 1944 በአሜሪካ ቺካጎ ከተማ ሃምሳ ሁለት ሀገራት በተሳተፉበት ጉባዔ የዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ሲቋቋም ከአፍሪካ ከተሳተፉ ሦስት ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች። ከዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት መመሥረት በቀናት ልዩነት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን አገልግሎት በሚል ስያሜ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት ጀርባ የማይተካ ሚና ሲጫወት ቆይቷል፡፡

ጠንካራ የሲቪል አቪዬሽን ተቋም ከሌለ ጠንካራ አየር መንገድ ሊኖር አይችልም፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል የአቪዬሽን ዘርፍም በሀገራችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት በተለይ ለቱሪዝምና ንግድ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርግ የቆየ ተቋም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ደህንቱ የተረጋገጠ የአየር ትነራንስፖርት እንዲኖር በማድረግ አየር የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከፍተኛ ዝናና ስኬት እንዲያስመዘግብ ከማድረጉም ባሻገር የአየር ትራንስፖርት ደህንነቱ ተጠብቆ ዘለቄታ ባለው ሁኔታ እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ አሁን ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓመት 17 ሚሊዮን መንገደኞችና ከ 750 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ዕቃን የማመላለስ አቅም የፈጠረውም የአቪዬሽን ዘርፉ በገነባው አስተማማኝ አቅም የተነሳ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ከሀገራት ጋር በሚያደርጋቸው ስምምነቶች መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ 141 ፤ በሀገር ውስጥ ደግሞ 23 መዳረሻዎች ያሉት ሲሆን በአምስት አውሮፕላኖች የተጀመረው በአየር የመጓጓዝ ሂደት አሁን ላይ 240 የሚሆኑ አውሮፕላኖች ተመዝግበው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ሁሉ ስኬት ጀርባ ደግሞ ደህንነትን በማስጠበቅ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ሚና የማይተካ ነው፡፡


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቅድሚያ ስጡ!

ብርሃን ፈይሳ

ብሄራዊ የስፖርት ማህበራት ሥራ አስፈጻሚዎች ምርጫን ተከትሎ ውዝግቦችና አግባብነት የሌላቸው አካሄዶችን መመልከት በኢትዮጵያ ስፖርት የተለመደ ነው። ለአንድ ስፖርት በእውቀት፣ በጉልበትና በገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ለእድገቱ ከመሥራት ባለፈ የተለየ ጥቅማ ጥቅም ይገኝበት ይመስል የሚከወኑ ተግባራት የሚያስተዛዝቡ ሆነዋል። በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከሚሰጥ ውክልና አንስቶ እስከ ድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ያሉት መጠላለፎች ስፖርቱን ለማገዝ ሳይሆን ከጀርባው የተለየ ዓላማ እንዳለ ያስጠረጥራል።

ኢትዮጵያ ስሟን በበጎ የተከለችበት የአትሌቲክስ ስፖርትም የዚሁ ገፈት ቀማሽ ከሆነ ሰነባብቷል። በዓለም አቀፍ ውድድሮች ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ የሚገኘውን ውጤት ጨምሮ በርካታ አስተዳደራዊና የአሠራር ችግሮች በተደጋጋሚ እየተወቀሰ ያለው ፌዴሬሽኑ በሥራ አስፈጻሚ ምርጫ ወቅት ደግሞ ሌላ መልክ ይይዛል።

ዘንድሮም ፌዴሬሽኑ አዲስ ፕሬዚዳንትና ሥራ አስፈፃሚ አባላትን ለመምረጥ በተቃረበበት በዚህ ወቅት የሚታዩ ሽኩቻዎች መጪውን የአትሌቲክስ ጊዜም ይበልጥ አስፈሪ እንዳይሆን ያሰጋል።

ተመራጮች ለስፖርቱ እድገት፣ ኢትዮጵያ ከአቻዎቿ ጋር ለሚኖራት ተፎካካሪነት እንዲሁም ሀገርን ለሚያስጠሩ አትሌቶች ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ ለሚቀመጡባት አንዲት ወንበር የሚጨነቁ መሆን የለበትም።

በጀግናውና ታላቁ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ የባዶ እግር ድል የተፈጠረው የኢትዮጵያና የአትሌቲክስ ስፖርት ዝምድና የተከበሩ ይድነቃቸው ተሰማ እና ንጉሤ ሮባን በመሳሰሉ የስፖርቱ ባለውለታዎች ተጠናክሮ ዛሬ መድረሱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ዘመኑ ከደረሰበት ሥልጣኔና የሌላው ዓለም አሠራር አንጻር የኢትዮጵያ አትሌቲክስ እየዳከረ የሚገኝበት አካሄድ ሽቅብ ሳይሆን ቁልቁል ይዞት እንዳይወርድ ያሰጋል። ከምድሯ ምርጥ አትሌቶችን ማፍራት የቀጠለችው ሀገር ፌዴሬሽኑን ለመምራት በሚደረግ የእርስ በእርስ ሴራና ሽኩቻ ቦታው በማይመጥነው ሰው እንዳይያዝ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ አሁን ላይ ባለፉት ዓመታት በተከናወኑ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በደል ደርሶባቸው ሲያነቡ የታዩ አትሌቶችና አለአግባብ የተገፉ አሠልጣኞችን ሮሮ ሰምቶ እንባቸውን የሚያብስ አመራር ነው የሚፈልገው።

በቅርቡ የሚካሄደውን የፌዴሬሽኑ 28ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔና እሱን ተከትሎ በሚከናወነው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ተሳታፊ የሚሆኑ እጩዎች ከቀናት በፊት ታውቀዋል። ይሁንና በትክክለኛው መንገድ ከመታወቃቸው አስቀድሞ ስሌታዊ በሆነ መንገድ እነማን በየትኛው ክልል አሊያም ከተማ አስተዳደር ሊወከሉ ይችላሉ የሚለው ይታወቅ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ አካሄዱ ትክክለኛውን መንገድ ሳይሆን ብልጣ ብልጥነት የተንሰራፋበትና ሥልጣንን ብቻ ዓላማ ያደረገ በመሆኑ ነው። በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈልም አንዱ ሌላኛውን ለማዳከም መታተራቸውም ለስፖርት ቤተሰብ በገሃድ እየታየ ይገኛል።

ብሄራዊ ፌዴሬሽኑን ለመምራት የሚደረገው ሽኩቻ እዚያው የሚወሰን ሳይሆን እንደየደረጃው እየወረደ ያለና በጉባዔው ድምጽ የመስጠት መብት ባላቸው ማህበራትንም ያዳረሰ መሆኑ ደግሞ የጉዳዩን አሳሳቢነት ይበልጥ ያጎላዋል።

ከዚህ ቀደም ፌዴሬሽኑ ይመራበት የነበረው የሥራ አስፈጻሚ አወቃቀር ስፖርቱን በማያውቁ ሰዎች መሆኑ ተጽዕኖ አድርጎብናል ያሉ አትሌቶች ከፍተኛ ንቅናቄ በመፍጠራቸው አትሌቶችን ወደ አስተዳደሩ ቦታ እንዲመጡ ማድረጉ የሚታወስ ነው። ይሁንና ባለፉት ሁለት የሥልጣን ዘመናት ከታዩ አንዳንድ መልካም ጅምሮች ባለፈ አስቀድሞ እንደተጠበቀው አዲስ ነገር ሊታይ አልቻለም። ስፖርቱን የመሩ አንጋፋ አትሌቶችም መሬት ላይ ሊወርድ የቻለ ውጤታማ አሠራር ተግባራዊ አለማድረጋቸው አትሌቱን ሊያስደስትም ሆነ እንደ ሀገር ውጤታማ ሊያደርግ አልቻለም። በመሆኑም ለመሪነት በስፖርቱ ውስጥ ማለፍ ብቻም ሳይሆን በእውቀት፣ በሥርዓት እና በእቅድ መሥራት የሚችል ሰው የግድ አስፈላጊ መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል።

ስለስፖርቱ እድገት የሚቆረቆሩና አቅም ያላቸው ሙያተኞች ወደፊት ከመምጣት ይልቅ ምርጫው ሳምንታት እየቀሩት በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የእጩዎች ማሳወቂያ ጊዜ አንስቶ በርካታ አነጋጋሪና ግራ አጋቢ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ቆይተዋል። ለእጩነት የሚቀርቡ አካላት ለአንድ ክልል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት አለማግኘትን ተከትሎ ሌሎች ክልሎችን እንደ አማራጭ መጠቀም ሁኔታ በግልጽ ታይቷል። ሕጉ የሚፈቅድላቸው ቢሆንም ከዚህ ቀደም በፌዴሬሽኑ ውስጥ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ያገለገሉ ነገር ግን ስፖርቱን ማሳደግ ያልቻሉ አካላትን በድጋሚ ለተመራጭነት ማቅረብ ደግሞ በክልሎች በኩል የታየ ግዴለሽነትና የሚያስታዝብ ሁኔታ ነው።

አትሌቶችም ሆኑ ሌሎች ከፌዴሬሽኑ በሥራ አስፈጻሚነት ምርጫ የቀረቡ አካላት ሥልጣን ለማግኘት ከሚያደርጉት ርብርብ ይልቅ ለስፖርቱ ተስፋ ሰጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው ለስፖርቱ የሚቆረቆሩ አካላት አበክረው ይገልጻሉ። በአትሌቶች ዘንድ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎችን ለመመለስና በቀጣይም መሰል ሁኔታ እንዳይፈጠር የሚያስችል አሠራርን መዘርጋትም ተጠባቂ ጉዳይ ነው። ፌዴሬሽኑ የሚሠራው ለስፖርቱ ሆኖ ሳለ የስፖርቱ ዋነኛ ተዋናዮች ግን አሁንም ድረስ ከለላ የሚሆናቸውንና በፍትሃዊነት የሚያስተናግዳቸው ባለማግኘታቸው ምክንያት ዓለም አቀፍ ውድድሮች በተካሄዱ ቁጥር እምባቸውንና ምሬታቸውን መመልከት የተለመደ ሆኗል። ጥቂት የማይባሉትም በዚሁ የአሠራር ብልሽት ምክንያት ተሰደው ለማያውቁት ሀገር በዜግነት ተሰልፈው ኢትዮጵያን ለመርታት በመፎካከር ላይ ይገኛሉ። በእርግጥ ይህ ሁኔታ ያማል ነገር ግን በትክክል ለአትሌቱ መቆምና መብቱን ማስከበር የቻለ አካል ማግኘት ለዓመታት ምኞት ብቻ ሆኖ ቀርቷል።

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባዔ አባላት መካከል አንዱ የአትሌቶች ማህበሩ ቢሆንም የሚመሩትን አካላት ለመምረጥ የሚያስችለው የድምጽ መጠን ግን ግራ አጋቢ ነው። በመሆኑም በጠቅላላ ጉባዔው ድምዳሜ ላይ የሚደረሱ ነገር ግን አትሌቱን ሊጎዱ የሚችሉ ውሳኔዎችን የማስቀየርም ሆነ እነሱን ያማከለ አሠራር ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችል አቅም ማዳበር አልቻለም። ይህም አትሌቶችን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ሁሌም መፍትሄ አልባ የሆኑ ቅሬታዎች ምንጭ ሊሆን ችሏል።

የአትሌቲክስ ስፖርት ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም በቁንጮነት ያስቀመጣት የሀገር ባለውለታ ስለመሆኑ በአያጠራጥርም። ለስፖርቱ የተመቻቸ የአየር ሁኔታ እና መልከዓ ምድር፣ እጅግ በርካታ ውጤታማና በማደግ ላይ ያሉ አትሌቶችም አሏት። በዚህም ምክንያት ታላላቅና ዓለም አቀፍ የሩጫ ውድድሮችን የማስተናገድ ሰፊ እድል አላት። ይሁንና እንኳን ውድድሮችን ለማስተናገድ የሚያስችሉ ጥራታቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ይቅርና አትሌቶች ዝግጅት ታዳጊዎችም ልምምድ የሚያደርጉበት ሥፍራ እንደልብ ለማግኘት ፈታኝ ነው። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ሀገር አቀፍ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ውድድሮችን ለማስተናገድ መሰናክሎችን ማለፍ አስገዳጅ መሆኑን ነው። በእርግጥ ፌዴሬሽኖች የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የማስገንባት ኃላፊነትና አቅም የላቸውም። ነገር ግን ከሕዝቡ የሚወከሉትና ዓላማውም በሃሳብ፣ በጉልበትና በገንዘብ ስፖርቱን ያግዛሉ በሚል የሚመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን በመቅረጽና የተለያዩ አካላትን በማስተባበር አንድ ርምጃ ማራመድ ይጠበቅባቸዋል።

ስለሆነም በዕጩነት የቀረቡ አካላት የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ለመዳን ያላቸውን ጊዜ ሊጠቀሙ ይገባል። ሥልጣን ከመያዝ ባለፈ በመጪዎቹ አራት ዓመታት በምን መልኩ ስፖርቱን ተፎካካሪ እንደሆነ ለማቆየት ያስችላል፣ ከእነማን ጋር መሥራት ውጤታማ ያደርጋል እንዲሁም መከተል ስለሚገባቸው የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ማሰላሰልና ከወዲሁ መዘጋጀት ይገባቸዋል። ከሥልጣንና ጥቅማ ጥቅም ሀገር ትልቃለችና የኢትዮጵያን አትሌቲክስ አስቀድሙ!!

# ተጠየቅ

# ‹‹ቤቶችን ለሚገነቡ የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መረጣ ግልጽ የሆነ መመሪያ የለም››

\- ኢንጅነር ፍቃዱ አለሙ

በአዲስ አበባ ቤቶች ኮርፖሬሽን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር

**መክሊት ወንድወሰን**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚስተዋሉ ችግሮች በግንባር ቀደምትነት የሚነሳው የቤት ችግር ነው:: በከተማዋ በርካታ የቤት ፈላጊ ነዋሪዎች መኖራቸው ይታወቃል:: መንግሥትም የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ በየጊዜው የተለያዩ አሰራሮችን ዘርግቶ ወደ ስራ ሲገባ ይስተዋላል::

ከእነዚህም ውስጥ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ አንደኛው ነው:: በዝቅተኛ ገንዘብ ነዋሪዎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ የተጀመረው ይህ ልማት ሁለት አስርት ዓመታት ቢቆይም፤ የጋራ መኖሪያ ቤት ለማግኘት የተመዘገቡ በርካታ ሰዎች አሁንም ቤት አላገኙም::

የጋራ መኖሪያ ቤት ለማግኘት የተመዘገቡ ሰዎች ቤት እንዲኖራቸው ለማስቻል እና አዳዲስ የቤት ፍላጎት ጥያቄዎችን ለመመለስ ከተማ አስተዳደሩ ምን እየሰራ ነው? ከቤቶች አቅርቦቱ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ ምን እየተከናወነ ነው? እና መሰል ጥያቄዎችን ለአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች ኮርፖሬሽን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለአቶ ፍቃዱ አለሙ አንስተን፤ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል::

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ቀደም ስነዋሪዎች የተሳሰፉ እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ይነሳባቸው የነበሩ ቤቶችን አጠናቆ ስሕብረተሰቡ ከማስረከብ አንጻር ምን አይነት ስራዎችን አከናወናችሁ?**

**ኢንጅነር ፍቃዱ፡-** ከለውጡ በፊት ተጀምረው የነበሩ የነባር ፕሮጀክቶች ግንባታ በአብዛኛው በያዝነው በጀት ዓመት የማጠናቀቂያ ስራቸው ተሰርቷል::

ተቋማችን አራት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አሉት:: ግንባታዎቹም በእነዚህ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይከናወናል:: የደቡብ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በምንለው በፉሪ እና በሃና አንድ ብሎክ፤ በበረከት ሳይት ደግሞ ስምንት ሕንፃዎች ሙሉ የማጠናቀቂያ ሥራዎች ያስፈልጋቸዋል ብለን ለይተናል::

በምስራቅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በ40/60፤ በበሻሌ ሳይት ሁለት ሕንጻዎች ፕሮጀክቶች፤ በቦሌ አያት ሁለት ደግሞ ሰባት ሕንጻዎች፤ በሰሜን ቅርንጫፍ ወይም 20/80 ቤቶች በተለይም አራብሳ ላይ ከ439 ሕንፃዎች በላይ አሉን:: ከእነዚህ ውስጥ ወደ ኋላ የቀሩትን ወደ 22 የሚሆኑ ሕንጻዎችን ለይተን የማጠናቀቂያ ሥራዎችን ሰርተናል::

አብዛኛው ሰው ቤቱ ከደረሰው በኋላ ትንሿንም ነገር እንደ ሥራ ይዞ ወደ ተቋማችን ይመጣል:: በእርግጥ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ መፈታት አለበት:: እንደ ተቋም ከውል አንጻር መሰራት ያለባቸውን ሥራዎች መሰራት አለባቸው የሚል አቋም ወስደን መጠናቀቅ የሚገባቸውን ሥራዎች አጠናቀናል::

በተለይ ደቡብ ቅርንጫፍ ላይ ሥራቸው ያላለቁ ዘጠኝ ሕንጻዎችን ሙሉ በሙሉ አጠናቀን ለነዋሪው ቁልፍ ሰጥተናል:: በተመሳሳይም ምስራቅ ቅርንጫፍ በሻሌ ሳይት ላይ ከሁለት ሕንጻ ውጭ በሳይቱ ያሉ የሕንጻ ሥራዎችን አጠናቀን አስረክበናል:: በዚህም በሁሉም 40/60 ቤቶችም ነዋሪዎች ገብተውባቸዋል:: ያልገቡ ነዋሪዎችም እንዲገቡ ማስጠንቀቂያ ሰጥተናል::

አራብሳም ላይ እንዲሁ ቤቶቹን ሙሉ በሙሉ የማጠናቀቂያ ሥራዎችን አከናውነን ለነዋሪዎች አስረክበናል:: በዚህ ሳይት ከቤቶቹ ማጠናቀቂያ ሥራ ጎን ለጎን የመሰረተ ልማት ጥያቄም ይነሳ ነበር::

እንደሚታወቀው የመሰረት ልማት ሥራው በእኛ ተቋም የሚሰራ አይደለም:: የመሰረት ልማት ሥራ ከመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ጋር አብሮ በቅንጅት የሚከናወን ነው:: የመንገድ፣ ውሃ፣ ፍሳሽ እና መብራት ሥራዎችን እንዲሰሩ በእኛ በኩል መጠናቀቅ የሚገባቸውን ሥራዎች ሁሉ ሰርተናል::

ከ40/60 ቤቶች መሰረተ ልማት ጋር በተያያዘ ከቦሌ አያት ሁለት ውጪ የመሰረት ልማት ጥያቄ የሚነሳበት ሳይት የለንም:: በበሻሌ ሳይት ከመብራት ዝርጋታ ጋር የተያያዘ ጥያቄ ይነሳ ነበር:: እነሱን ከሚመለከተው አካላት ጋር ተነጋግረን ጊዜያዊ የመብራት አቅርቦት እንዲያገኙ ተደርጓል::

አሁን ላይ በሳይቱ መካከለኛ እና ከፍተኛ የኃይል መስመሮች እየተዘረጉ ነው:: ነገር ግን አሁንም ከእኛ የሚጠበቁ የፓምፕ እና የሊፍት ሥራዎች አሉ:: እነሱንም ከመሰረተ ልማቱ ስራ ጋር ጎን ለጎን እየሰራን እንገኛለን::

ከመሰረተ ልማት ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ጥያቄዎችን ለመፍታት ከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው:: በዚህም በቦሌ አያት ሳይት ሁሉም የመሰረተ ልማት ተቋማት ገብተው ሥራዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ እያካሄዱ ነው::

አራብሳ ላይ እንዲሁ የመንገድ ጥያቄ ነበር:: የመንገድ ሥራ ሲሰራ ከሁሉም የመሰረተ ልማቶች ጋር ይያያዛል:: ከውሃ፣ ከመብራት እና ከሌሎች የመሰረት ልማት መስመር ዝርጋታ ሥራዎች ጋር አብሮ የሚሄድ ነው::

አሁን ላይ በሳይቱ በሚገኙ ቤቶች ሰዎች እየኖሩባቸው በመሆኑ የፍሳሽ፣ የውሃ እና የመብራትም አገልግሎቶች በግዜያዊነት እየተሰጠ ይገኛል:: አሁን ላይ የመንገዱን ሥራ ውል ገብቶ ሲያከናውን የነበረውን ተቋራጭ የመንገዶች ባለስልጣን ውሉን በማቋረጥ የመንገድ ሥራውን ራሱ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እየሰራ ነው:: በሁለተኛው ሩብ የበጀት ዓመት ሥራውን አጠናቀን እንወጣለን::

**የሊፍት ገጠማ ሥራ እያከናወንን ያለነው ለአሁኖቹ ግንባታዎች ብቻ አይደለም:: ከዚህ በፊት ለተገነቡ ሕንጻዎች ጭምር ነው**



**አዲስ ዘመን፡- ነዋሪዎች በተደጋጋሚ የሊፍት እና የፓንፕ ጥያቄ ሲያነሱ ይስተዋሳል፤ ይሄንን ችግር በተቋማችሁ ስመፍታት ምን እየሰራችሁ ነው?**

**ኢንጅነር ፍቃዱ፡-** በጣም ብዙ ሕንፃዎች አሳንሰር /ሊፍት/ እና የውሃ ፓምፕ ያስፈልጋቸዋል:: ሥራው ከፍተኛ የገንዘብ ወጭን የሚጠይቅ ነው:: ለምሳሌ የደቡብ ቅርንጫፍን ብቻ ብንመለከት በቅርንጫፉ ከ1257 በላይ ሕንጻዎች አሉ:: ከእነዚህ ውስጥ ከ557 በላይ የሚሆኑት ሕንጻዎች ሊፍት የሚፈልጉ ናቸው:: በተመሳሳይ ሊፍት የሚፈልጉት ሕንጻዎች ፓምፕም ይፈልጋሉ::

በሰሜን ቅርንጫፍ ከ587 በላይ ሕንፃዎች አሉ:: ከእነዚህ ውስጥ 357 የሚሆኑት ሕንጻዎች አሳንሰር እና ፓምፕ የሚፈልጉ ናቸው:: ከ40/60 ፕሮጀክትም 356 የሚሆኑት ሕንጻዎች ሁሉም ከጂ+7 በላይ ስለሆኑ ሁሉም ፓምፕ እና አሳንሰር ይፈልጋሉ:: በውሉ መሰረት ለሁሉም ሕንጻዎች የመሰረተ ልማቶቹ ሊሟሉላቸው ይገባል:: ለሁሉም ሕንጻዎች ሊገጠሙላቸው የሚገባቸው አሳንሰሮች ደግሞ ‹‹ደብል›› አሳንሰሮች ናቸው:: ለ40/60 ቤቶች ብቻ 712 አሳንሰር እና 356 ፓምፕ ያስፈልጋል::

ተቋሙ ከበፊት ጅምሮ ሲንከባለል የመጣ የባንክ እዳ እና ወለድ አለበት:: ልክ ለውጡ ሲመጣ 54 ቢሊየን ብር እዳ ነበረበት:: ነገር ግን ለነዋሪዎች ከሚተላለፉ ቤቶች እና የንግድ ቤቶችን ለጨረታ በማውጣት ተቋሙ ከነበረበት እዳ ወደ 32 ቢሊየን ብር ዝቅ ማድረግ ተችሏል::

በተያያዘም እነዚህ ያላለቁ ሥራዎች ከፍተኛ የሆነ ገንዘብን ይጠይቃሉ:: ሊፍት በጣም ውድ ነው:: ከዶላር ጭማሪው ጋር ተያይዞ አንድ ሊፍት ከዚህ ቀደም ከነበረው ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ጭማሪ አሳይቷል:: ይሁን እንጂ የነዋሪዎችን ችግር ለመቅረፍ አሁን ላይ የተወሰኑ ሊፍቶችን ለመግዛት ጨረታ አውጥተን በሂደት ላይ እንገኛለን::

ከእነዚህ ውስጥ ለ40/60 ፕሮጀክቶች የሚሆኑ 336 ሊፍቶች ሀገር ውስጥ ገብተዋል:: 70 የሚሆኑ ሊፍቶችን ደግሞ መገጣጠም ስራ ተጀምሯል:: ተቋማችን ከሊፍት አቅራቢው ጋር የተወሰነ ችግር ነበረበት:: ነገር ግን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በጋራ በመሆን ችግሩን ፈተናል::

ለ20/80 ፕሮጀክቶች ሊፍት ለማቅረብ ጨረታ ያሸነፉ አራት ድርጅቶች ናቸው፤ ከእነዚህ መካከል አሁን ላይ ሥራቸውን በአግባቡ እየሰሩ ያሉት ሁለቱ ብቻ ናቸው:: ከሁለቱ አንደኛው ደግሞ የሊፍት ገጠማ ሥራውን አገባዷል፤ አሁን ላይ በጨረታ ካሸነፉቸው ሕንፃዎች ሁለት ቀርተውታል::

የሊፍት ገጠማ ሥራ እያከናወንን ያለነው ለአሁኖቹ ግንባታዎች ብቻ አይደለም:: ከዚህ በፊት ለተገነቡ ሕንጻዎች ጭምር ነው:: አሁን ላይ በነባር ፕሮጀክቶች የነበረውን የሊፍት ገጠማ ችግር አብዛኛውን እየቀረፍን ነው::

ሁለተኛው የሊፍት አቅራቢ ድርጅት ደግሞ ማቅረብ ከነበረበት 230 በላይ ሊፍቶች ግማሽ ያህሉን አቅርቧል:: ከ120 በላይ የሚሆኑ ሕንጻዎች የገጠማ ሥራዎችን ተሰርቷል:: ቀሪ ሥራዎችን ደግሞ በፍጥነት እንዲያጠናቅቅ ለማስቻል በጋራ እየተነጋገርን እና እየሰራን ነው:: ሶስተኛው እና አራተኛው ድርጅቶች ግን በስራ ላይ አይደሉም::

በመሆኑም ከአቅራቢዎቹ ጋር በውሉ መሰረት እየተነጋገርን ነው:: እነሱ ጊዜ እንዲሰጣቸው እየጠየቁን ነው:: ነገር ግን ይሄንን ለማድረግ የዳሰሳ ጥናት መስራት ያስፈልጋል::

ለበሻሌ ሳይት አሳንሰር ለማቅረብ የተዋዋልነው ድርጅት በውሉ መሰረት ስራዎችን እያከናወነ ባለመሆኑ ውል አቋርጠናል:: በመሆኑም በሻሌ ሳይት አዲስ ጨረታ ለማውጣት በሂደት ላይ ነን::

**አዲስ ዘመን፡- ነዋሪዎች ቅሬታ ከሚያነሱበት ጉዳዮች በዋናነት የሚጠቀሰው በእጣ ያገኘነው ቤት በውሉ መሰረት ተጠናቆ አይሰጠንም የሚል ነው:: ከዚህ አንጻር ቤቱ ስንት በመቶ ሲጠናቀቅ ነው ስነዋሪዎች የሚተሳለፈው?**

**ኢንጅነር ፍቃዱ፡-** ፕሮጀክቶቹ ሲታቀዱ 20/80 መካከለኛ ገቢ ላላቸው፤ 10/90 ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## ‹‹ቤቶችን ለሚገነቡ የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች...

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

ላላቸው በሚል ነው:: ከአንደኛ እስከ 14ኛ ዙር በነበረው እጣ የቤቱ ግንባታ 80 በመቶ ሲጠናቀቅ ለነዋሪዎች የተላለፈ ነው::

ነዋሪዎቹ ቤት ለማግኘት ከጠበቁበት ግዜ አንጻር ግንባታው ጥንቅቅ ያለ ሙሉ ቤት ይፈልጋሉ:: ነገር ግን እኛ እንደ መንግሥት ቤቶቹን የምናስተላልፈው በድጎማ፤ በካሬ 8ሺ ብር ባልሞላ ገንዘብ ነው:: ይህ ማለት ባለ ሶስት መኝታ ቤት እድለኛ የሆነ ሰው አጠቃላይ ክፍያ ሰባት መቶ ሺህ ብር ያልሞላ ነው:: ነገር ግን እኛ ቤቶቹን ባስተላለፍነው በጥቂት ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ዋጋ ሊሸጡት ይችላሉ::

አንድ ሴራሚክ በካሬ ከ1ሺ ብር በላይ በሆነ ዋጋ ገዝተን ቤቱን የምናስተላፈው ግን ያንን ፈጽሞ መመለስ በማይችል ዋጋ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ብድር ስለነበረብን ለፕሮጀክቶቹ እነዚህ አይነት ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ንግድ ባንክ አላበድርም አለን:: ንግድ ባንክን እንደ አንድ አትራፊ ድርጅት ያደረገው ልክ ነው::

በፊት 20/80 ቤቶች ላይ ሊሾ እንሰራለን፤ የመጸዳጃ ቤት እና የወለልም ግድግዳም ሴራሚክ፤ የመጸዳጃ ቤት መቀመጫ እንሰጣለን እና መብራትም እንገጥማለን:: ከ2015 ጀምሮ ለሚተላለፉ ቤቶች ግን እነዚህን ሥራዎች ለነዋሪዎቹ ብንተዋቸው የሚል አቋም ያዝን::

ይህን ተከትሎ በእጣ ያልተላለፉ ምን ያህል ቤቶች እንዳሉን እና ምን ያህል ደግሞ ንግድ ቤቶች እንደሆኑ ከባንኩ ጋር ኦዲት አደረግን:: ከኦዲት በኋላ ባንኩ ለቀሪ ሥራዎች ማጠናቀቂያ አምስት ቢሊዮን ብር ለቀቀልን:: ያንን አምስት ቢሊየን ብር ለነበሩን 139ሺ ቤቶች እንዴት መጠቀም እንዳለብን አቀድን::

ነገር ግን የነበረን አምስት ቢሊየን ብር ግንባታቸው ላልተጠናቀቀ 139ሺ ቤቶችን ሥራ ለማጠናቀቅ በቂ አልነበረም:: በወቅቱ የቤቶቹ ግንባታ በማጠናቀቅ ለነዋሪዎች ለማስተላለፍ 17 ቢሊየን ብር ያስፈልገን ነበር:: ቤት ተመዝጋቢዎች ደግሞ እየቆጠቡ እየጠበቁን ነው:: በዚህ በኩል ደግሞ አንዳንዶቹ ቤቶቹ ገና ‹‹ስትራክቸር›› ላይ ነበሩ::

በዚህም ከ20/80 ፕሮጀክቶች ዘጠኝ ሥራዎች 40/60 አስራ አንድ ሥራዎች እንዲቀነሱ በቦርድ አስወሰንን:: ቦርድ ውሳኔውን የወሰነው ተቋማችን ባቀረበው ጥናት መሰረት ነው:: ለምሳሌ እኛ ሰርተን ከሰጠን በኋላ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው ሰው የሊሾ ስራው እንደገና አፍርሶ ነው የሚሰራው:: በር እና መስኮትም እንዲሁ አጥንተን ቢቀሩ የሚል ምክረ ሃሳብ አቀረብን::

እነኝህን አስቀርተን የመሰረተ ልማት ዝርጋታውን ሊያግዝ የሚችል ሥራ ላይ እና የደረጃ ሥራዎች ላይ ለማተኮር አቀድን:: ከዚያ በኋላ ቤት ለደረሳቸው ነዋሪዎች ስለጉዳዩ የማሳወቅ ስራ ሰራን::

**አዲስ ዘመን፡- አዳዲስ ግንባታዎችንስ ከመገንባት አኳያ ምን ታስቧል፤ ምን እየሰራችሁ ነው?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** በአዳዲስ ግንባታ ዙሪያ ‹‹የማስ ሀውሲንግ›› ስራ እየሰራን አይደለም:: ምክንያታችን ደግሞ ገንዘብ ነው:: አሁንም ተቋሙ 32 ቢሊየን ብር አካባቢ እዳ አለበት:: በቀን ስምንት ሚሊዮን ብር ወለድ እንከፍላለን:: ይሄንን እዳ ሳንመልስ አዲስ በጀት ማግኘት አንችልም::

ስለዚህ ለአዳዲስ ግንባታ ለመጀመር ስለምንቸገር ተብሎ በከተማ አስተዳደሩ ጥናት ተጠንቶ ሌሎች አማራጮችን ለመጠቀም ጀምረናል:: ከዚህ ውስጥ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስትራቴጂ አንደኛው ነው:: በዚህም ከ22 አልሚዎች ጋር የመንግሥት እና አጋርነት ውል ተፈራርመናል:: ሰባቱ አልሚዎችም ወደ ሥራ ገብተው ግንባታ ጀምረዋል::

በዚህ ከ120 ሺ በላይ ቤቶችን ለመገንባት አቅደናል:: ከዚህ ውስጥ 60ሺ ቤት የሚሰራው በኦቪድ ሪል እስቴት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በእኛ መስራት የምንችለውን ካፒታል በጀት አስበጅተን አዳዲስ ግንባታዎችን መገንባት ነው:: ከዚህ አንጻር አየር ጤና እና ኮልፌ በዚህ ዓመትም ሶስት ሕንጻዎችን የሰራን ሲሆን ጀርመን አደባባይ ደግሞ ከ780 በላይ ቤቶችን የያዙ ስምንት ሕንጻዎችን እየሰራን ነው::

በተመሳሳይ በቱሉ ዲምቱ አንድ ሕንጻ አለን፤ አራብሳ ላይ 390 ቤቶችን ሶስት ሕንፃዎች መገንባት ጀምረናል:: አሁን እናስጀምራለን ብለን ያሰብናቸው ከ2ሺህ በላይ ቤቶች አሉ:: ከዚህ በተጨማሪም በከተማዋ ያለውን የቤት ችግር ለመቅረፍ በማህበር የማደራጀት አማራጮችን እየተጠቀምን ነው::

> **በመንግሥት እና የግል አጋርነት ሂደት ውስጥ ባለሃብቱ ገንዘብ ያመጣል:: መንግሥት ደግሞ የመሬት እና ቴክኒካል ድጋፍ ሥራዎችን ይሰራል**

**አዲስ ዘመን፡- ነባር የግንባታ ሂደቶች ሃብት እና ጊዜን የሚያባክኑ ናቸው:: እነሱን ለማዘመን ምን አይነት ሥራዎችን ሰርታችኋል?**

**ኢንጅነር ፍቃዱ፡-** በፊት የነበረው አካሄድ በጣም አሰልቺ እና ለምዝበራም የተጋለጠ ነበር:: ብዙ እዳ እንዲኖርብንም ያደረገው ይሄው አካሄድ ነው:: የአቅራቢነቱንም ሆነ የመቆጣጠሩን ሥራ የሚሰራው በመንግሥት ነበር:: ከ2012 ዓ.ም በኋላ ግን ሥራውን ለኮንትራክተሩ ሰጥተን ነው የምንገባው:: ይሄ አካሄድ በራሱ በጣም ብዙ ጊዜ ቀንሶልናል::

ለምሳሌ በኮልፌ ከ330 በላይ ቤቶች በኮንትራክተር የተሰሩ ናቸው:: የአሰራር እና የቁጥጥር ሂደቱን በማዘመናችን እና በመቀየራችን በአስር ወራት ውስጥ ተሰርተው እንዲጠናቀቁ ሆኗል:: በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ወርቁ ሰፈር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ላይ ተገጣጣሚ ቤቶችን ለመስራት ከኢትዮጵያን ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ጋር ውል ፈጽመን ነበር::

በውሉ መሰረት ያስገነባናቸው በርካታ ጂ+4 ቤቶችን አጠናቀን ለልማት ተነሽዎች መስጠት ተችሏል:: እነዚህ ቤቶች በጣም የሚያምሩ እና በአጭር ጊዜ የተሰሩ ናቸው::

ልደታ እና ሪቼ አካባቢም ባለፈው ዓመት በ67 ቀናት ውስጥ አራት ጂ+11 ቤቶችን አጠናቀናል:: አሁንም በግንፍሌ ላይ በስድስት ወር ከአንድ ሺህ በላይ ቤቶችን ለመስራት አቅደናል::

**አዲስ ዘመን፡- እጃችሁ ላይ ምን ያህል ተመዝግቦ እጣ ያልደረሰው ቤት ፈላጊ አለ? ለእነዚያ ተመዝጋቢዎችስ በምን ያህል ግዜ ቤቱን ጨርሳችሁ ለማስረከብ አቅዳችኋል?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** አሁን ላይ ከአምስት መቶ ሺህ በላይ የሚሆኑ ተመዝጋቢዎች ቤት እየጠበቁ ነው:: ዓለም ባንክ ባጠናው ጥናት መሰረት አዲስ አበባ ላይ ብቻ ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ አዲስ የቤት ፍላጎት አለው:: ነገር ግን ይህን ቤት እኛ መገንባት አንችልም:: ምክንያቱም አሁን ላይ እኛ ‹‹ማስ ሀውሲንግ›› እየገነባን አይደለም:: ለዚያም ነው ተቋማችን የአሰራር ሂደቶችን እና አማራጮችን እንዲሁም ስልቶችን መቀየር ያስፈለገው::

ከዚህ በፊት 54 ማህበራት ተደራጅተው ከ5 ሺህ በላይ ቤቶችን ለመገባት በሂደት ላይ ናቸው:: አሁንም ማህበራትን በማደራጀት እንዲሁም ለማህበራቱ መንግሥት የመሬት አቅርቦት እያከናወነ ነው:: በተጨማሪም ማህበራቱ ከባንኮች ብድር የሚገኙባቸውን መንገዶች የማመቻቸት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል::

በመንግሥት- የግል ጥምረቱ እየተገነቡ ካሉት 120 ሺህ በላይ ቤቶች 30 በመቶ የሚሆን የመንግሥት ድርሻ ነው:: ስለዚህ ቅድሚያ እጣ የምናወጣው ለተመዘገቡት ነው:: በካፒታል በጀት የምንገነባውን ደግሞ በኪራይ እና በሽያጭ እናስተላልፋለን::

**አዲስ ዘመን፡- በመንግሥት የግል አጋርነት ባለሃብቱን ብቻ ትርፍ የሚያጋብስበት እንዳይሆን ከመስራት አኳያ ምን የተለየ አካሄድ እየሄዳችሁ ነው?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** በመንግሥት እና የግል አጋርነት ሂደት ውስጥ ባለሃብቱ ገንዘብ ያመጣል:: መንግሥት ደግሞ የመሬት እና ቴክኒካል ድጋፍ ሥራዎችን ይሰራል:: ስለዚህ ባለሃብቱ ብቻ ተጠቃሚ እንዳይሆን ጠበቅ ያለ ውል እናስራለን:: ችግር ቢፈጠር እንኳን በውሉ መሰረትም ወደኋላ ተመልሰን መጠየቅ የሚያስችል አሰራር ዘርግተናል::

ለባከነው ጊዜ መሬቱ ቢሰራበት ለሚያወጣው ዋጋ እና አጠቃላይ ተያያዥ ነገሮችን መጠየቅ የሚያስችለንን ውል ነው የምናስረው:: ስለዚህ በዚህ በኩል ብዙ ስጋት የለንም:: አሁንም መሬቱን ተረክበው ወደ ስራ ባልገቡት ላይ ወደ ሕጋዊ እርምጃ መሄዳችን የማይቀር ነው::

ከማስተላለፉም ጋር ተያይዞ እንዲሁ በመንግሥት እና ግል አጋርነት ይተላለፉ ለሚለው መመሪያ የማስተካከል ስራ እየተሰራ ነው:: ለምሳሌ ኣቪድ ከሚሰራው 60 ሺ ቤት ውስጥ 18ሺ ቤት የመንግሥት ነው:: ይሄንን ቤት ለተጠቃሚው በእጣ እናስተላልፈዋለን::

**አዲስ ዘመን፡- ብልሹ አሰራሮችን ከመቀነስ አንጻር የሰራችኋቸው ስራዎች አሉ፤ በተጨባጭ ምን ምን ናቸው?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** እንደ ሀገር በተጠናው ጥናት የኮንስትራክሽ ዘርፉ ለብዙ በብልሹ አሰራሮች የተጋለጠ ነው:: ከዚህ በፊት የነበረንን አሰራር በመቀየራችን በርካታ ብልሹ አሰራሮችን ለመቀነስ ችለናል:: እንደዚህም ሆኖ ግን በምንፈልገው ልክ መቀነስ ባለመቻሉ ተቋማችን ላይ የሪፎርም ስራዎችን ሰርተናል:: አዋጅ እንዲወጣና መመሪያዎችም እንዲሻሻል የማድረግ ሥራዎችን ሰርተን አሁን ላይ ፍትህ ሚኒስቴር እንዲያጸድቅልን እየጠበቅን ነው::

ከተቋሙ አደረጃጀቱ ጋር በተያያዘ ተቋሙ ከ22 በላይ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የነበሩት ስለነበር ያንን ማስተዳደር በራሱ በጣም አስቸጋሪ ነበር:: አሁን እነሱን ሰብስበን አራት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አድርገናቸዋል::

የሰው ኃይላችንም ፈተና ተፈትኖ እንዲገባ በማድረግ ብቁ የሆኑ ሰራተኞችን መድበናል:: በአጠቃላይ በአሰራር፤ በመመሪያ እና በአደረጃጀት ሪፎርም አድርገን አብዛኛውን ብልሹ አሰራር ለመዝጋት እየሞከርን ነው::

ግን ሁሉም ቦታ ሰው ነው የሚሰራው፤ ስለዚህ በየእለቱ ክትትል ያስፈልገዋል:: ክትትሉ ፍሬአማ እንዲሆን ለማስቻል ተቋሙ በዳይሬክቶሬት ደረጃ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የጸረ ሙስና ክፍል አቋቁሟል፤ እርምጃዎችንም እየወሰደ ነው ::

**አዲስ ዘመን፡- ተቋራጮችን ስትመርጡ በምን መመዘኛ ነው? የመስራት አቅማቸውንስ እንዴት ትለካላችሁ ?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** ቤቶችን ለሚገነቡ የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መመሪያ የለም:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ሪፎርም ስናደርግ ጥናት አጥንተን አቅርበናል:: በቅርቡ ጸድቆ ሥራ ላይ ይገባል የሚል እምነት አለን::

መመሪያው እስከሚወጣ ብለን ከመመሪያ ረቂቅ ላይ ቼክ ሊስት ወስደን እንዴት ይመረጥ የሚለውን እየሰራንበት ነው:: ባለፈው ዓመትም በዚሁ አካሄድ ምዝገባ አድርገናል::

ወደ ሥራ ካስገባናቸው በኋላ የጥራት ቁጥጥር የሚያደርጉ ክፍሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቻችን ላይ አሉን:: ከማዕከልም እንዲሁ ግንባታና ጥራት ቁጥጥር የሚባል ዳይሬክቶሬት አለን:: በዚህ ዳይሬክቶሬት ውስጥ መሃንዲሶች አሉ:: እነሱ ክትትል ያደርጋሉ:: ክትትሉን ስናደርግ የጥራት ጉድለት ሲገኝባቸው በውሉ መሰረት እርምጃ እንወስዳለን:: ነባሮቹ ላይ ግን በጣም ብዙ ጉድለት ነበር:: አዳዲሶቹ ላይ ግን እንደዚህ አይነት ችግር ገጥሞን አያውቅም::

**አዲስ ዘመን፡- በጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የኮሚናል ግንባታዎች ቀመዋል:: ይህም የሰዎችን ማህበራዊ ሕይወት እንዳይጠናከር ለማድረግ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው የሚሉ ቅሬታዎች አሉ:: ስዚህ የእርስዎ ምላሽ ምንድነው?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** እውነት ነው ግንባታው ቀርቷል:: ግን የሰዎችን ማህበራዊ ሕይወት እዳይጠናከር ታሳቢ ተደርጎ አይደለም:: የኮሚናል ቤቶች ግንባታ ከ2007 ዓ.ም በኋላ የቆመ ነው::

ግንባታው የቀረበት ዋናው ምክንያት፤ ጥናት ተደረገና ለኮሚናል ግንባታ የሚወጣው ገንዘብ ትልቅ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: ነገር ግን አብዛኛው ጊዜ በኮሚናሎች ነዋሪው ተጠቃሚ አይሆንበትም:: በጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚገኙ ኮሚቴዎች ለራሳቸው አከራይተው ሲጠቀሙበት ይታያል:: ግንባታው የቆመው በእነዚህ ምክንያቶች እንጂ ሌላ አጀንዳ ስላለን አይደለም::

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚናል የሚያከራይ ኮሚቴ ካለ ያንን ኮሚቴ ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም ነበር? እንዴት ለሕዝብ ይጠቅማል የተባለ ግንባታ እንዲቆም ይደረጋል?**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** ከዚህ ጋር ተያይዞ በርካታ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ይነሳሉ:: አሁን በቢሮ በኩል ምን ማድረግ እንችላለን? እንደ አዲስ ብናስጀምር ይሻላል? ለነዋሪው ብንፈቅድለት እና በራሱ ቢገነባው የሚለውን ለመመለስ በአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ቢሮ በኩል ጥናት እየተደረገ ነው:: ጥናቱ እንዳለቀ ውሳኔውን ይሰጡናል::

መጀመሪያ የተወሰነው ውሳኔ በራሱ ትክክል ነው ወይ? የሚለው ለመፍታት ጥናት ይፈልጋል:: ምክንያቱም እንደተባለው ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለራሳቸው አገልግሎት የሚጠቀሙ ነዋሪዎች ስላሉ:: በኛ በኩል ከአስፈላጊነቱ ጋር ምንም ጥያቄ የለንም::

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ::**

**ኢንጅነር ፈቃዱ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

ዶህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ትልቅ አዕምሮን የሚፈልግ ክቡር ሞያ

**ደበሎ ካሳ**

ጋዜጠኝነት ክቡር ሞያ ነው፡፡ ክቡርነቱም ክቡር ከሆነው ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ በመሆኑ ነው፡፡ ጋዜጠኝነት ክቡር ብቻ አይደለም ታላቅም ነው፡፡ መነሻውም መድረሻውም የሰውነት ተፈጥሮ ነው! ዓላማው ሕዝብና የሕዝብ ጥቅምን ማስጠበቅ ነው፡፡

ተልዕኮው ሰውን አስቀድሞ በሰዎች መካከል እኩልነት፣ ፍትህ፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ እንዲኖር፤ የሃገርና ሕዝብ ዕድገትና ብልጽግና እንዲረጋገጥ መንገድ ማቃናት ነው፡፡ ከዚህ የሚበልጥ ትልቅ ዓላማም የለም፡፡ ትልቅ ስም ብቻ ሳይሆን ትልቅ ኃላፊነትን የሚያሸክምም ነው፡፡ በሌላ በኩል ጋዜጠኝነት ሕዝብን ያክል ነገር የመምራት ትልቅ ኃላፊነት የተጣለበት የመንግሥትነት ሚናም የተሰጠው ሞያ ነው፡፡

ሚና ብቻ አይደለም፤ ጋዜጠኝነት በራሱ አራተኛ መንግሥት ነው፡፡ መንግሥትነት ደግሞ ትልቅም ከባድም ነገር ነው፡፡ መንግሥትነት ደግሞ ቀላል ነገር አይደለም፣ እንደ መንግሥትነት ከባድ ነገርም የለም፡፡ "መንግሥትና እግዚአብሔር አንድ ናቸው" የሚለው የአገሬ ሰው አባባልም ዝም ብሎ የተባለ አይደለም፡፡ ትልቅ ሚስጥርን ያዘለ ዕፁብ ድንቅ የሚያስብል አስተሳሰብን የተሸከመ ፍልስፍና ነው፡፡

ለምን ቢባል በዚህ አባባል ውስጥ "አንድ ናቸው" የሚለው ተለዋጭ ዘይቤ የሁለት ታላላቅ አካላትን ማንነት ማሳየት ዋነኛ ዓላማው ነው - የመንግሥትንና የእግዚአብሔርን የግብር ተነጻጻሪነት! ታዲያ እዚህ ጋር "መንግሥትና እግዚአብሔር የሚመሳሰሉበት (አንድ የሚሆኑበት) ማለትም የግብር ተመሳስሎአቸው በምንድር ነው?" የሚለውን ጥያቄ ስንመልስ ነው የሚስጥሩ ሚስጥር የሚገለጽልን፡፡

ታላቁ ሚስጥር "እግዚአብሔር የዓለሙን ፍጥረት ከፈጠረ በኋላ ዝም ብሎ ያለ ሕግ አልተወውም የሚል ነው"፡፡ የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ፣ ሕይወት ያለውንም ሕይወት የሌለውንም፣ የሚታየውንም የማይታየውንም፣ ሰማይንም ምድርንም የሚያስተዳድርበት ሕግና ሥርዓት አበጅቶለታል፡፡ ዳር ድንበር፣ ወሰንና መዳረሻ፣ ቅርጽና መጠን፣ ልኬት ሕልቆ መሳፍርት በሌለው አጽናፈ ዓለም ውስጥ ያለውን ፍጥረት ሁሉንም እንደየፍጥርጥሩ በሥርዓቱና በአግባቡ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

ይህም ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ለሚመራውና ለሚያስተዳድረው ፍጥረቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ አንዳችም ሳያስቀር አሟልቶ ያቀርባል፡፡ ቀንና ሌሊትን፣ ፀሃይና ጨረቃን፣ ክረምትና በጋን እያፈራረቀ ፍጡራኖቹን ይመግባል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ሳይጠየቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰማይና ምድርን መምራትና ማስተዳደር ታላቅ ስልጣን ብቻ ሳይሆን ታላቅ ኃላፊነትም በመሆኑ ነው፡፡

መንግሥትም እንደ እግዚአብሔር ሁሉ ከባዱንና ትልቁን "የመምራትና የማስተዳደር ስልጣን" የተሸከመ መሆኑ ነው ትልቅ ያስባለው፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም ከፊት ሆኖ በበላይነትና በአዛዥነት መምራትና ማስተዳደር ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ እግዚአብሔር ሁሉ ያለ ማንም ጎትጓችነትና ጠያቂነት የሚመሩትን አካል ደህንነትና ጥቅም በአግባቡ አስጠብቆ መገኘትን ግድ ይላል፡፡

በሌላ አባባል ከታላቁ ስልጣን ጀርባ ከባድ ተጠያቂነት መኖሩንም አውቆ ኃለፊነትን በአግባቡ መወጣትን ይጠይቃል፡፡ ሕዝብን የመምራትና የማስተዳደር ስልጣንና ኃላፊነት ወይም የመንግሥት ተግባር ምን ያህል ከባድ መሆኑን ለመግለጽ "መንግሥትና እግዚአብሔር አንድ ናቸው" ከሚለው የእኛው ኢትዮጵያዊ አባባል በላይ የተሻለ ማሳያ ሊኖር እንደማይችል የሚያስረግጥ ነው፡፡ ዓረፍተ ነገሩ ከአባባልነትም በላይ ግሩም ድንቅ የሆነ ሚስጥር በውስጡ አምቆ የያዘ ጥልቅ ፍልስፍና ነው የተባለበት ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

መንግሥትነት ይህን ያህል ትልቅና ከባድ ነገር ከሆነ መንግሥት ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ማለትም መንግሥት በስልጣኑ እንዳይባልግና ሕዝብን እንዳይበድል የመንግሥትን አሠራር የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት ጋዜጠኝነት ደግሞ ከመንግሥትነትም በላይ ታላቅና ከባድም ነው!

ይሁን እንጂ ሃቁ ይኼ ሆኖ ሳለ የጋዜጠኝነት ሞያ የታላቅነቱን ያህል የሚያሸክመውን ታላቅ ኃላፊነት የራሱ አካላት ከጋዜጠኝነት መርህ ፍጹም በተቃራኒው ሲጓዙ በተለያዩ ጊዜያት በዓለማችን ላይ ተስተውለዋል፡፡ ለሰውና ለሰው ደህንነት ከሚታገለው ከእውነተኛው የጋዜጠኝነት ሞያ የወጡት እነዚህ አካላትም ከዓላማው በተቃራኒ ሞያውን ለሰው ጥፋት ሲጠቀሙበትም ተስተውሏል፡፡

ለሰው ልጆች ሕይወትና ደህንነት ዘብ የሚቆመው ታላቁ ሞያም ለታላቅ ጥፋት መሳሪያ ሆኖ ሲያገለግልም የሰው ልጅ በዓይኑ በብረቱ የተመለከተበት ታሪክም የዓለማችን የቅርብ ትውስታ ነው፡፡ አሁን ላይ በእኛ ሃገር በተለይም ከለውጡ በኋላ ሃገራችን ውስጥ ባሉ አንዳንድ የሚዲያ ተቋማት የምናስተውለው ሁኔታም ይህንኑ ነው፡፡

ሕዝብና የሕዝብን ጥቅም በማስቀደም፣ በሰዎችና በሕዝቦች መካከል እኩልነት፣ ፍትህ፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ የሃገር ዕድገትና ብልጽግና እንዲመጣ በመስራት ፋንታ ጋዜጠኝነት ለብዙ ሺ ዘመናት አብሮ በኖረ ወንድማማች ሕዝብ መካከል በክፋት ፈላስፎች የተፈበረከ ሃሰተኛ የጥፋት ታሪክን ለማስተማር እያገለገለ ይገኛል፡፡

በተለይም ድህረ ዘመናዊነትና ቁሳዊነት ከፈጠረው ልቅነትና ሞራላዊ ዝንፈት ጋር ተያይዞ ክቡሩ ሞያ ጋዜጠኝነት ጥላቻን የሚሰብኩ፣ ወንድም ወንድሙን እንዲያፈናቅል፣ እንዲገድል አመራር የሚሰጡ ከአውሬም ከሴጣንም የሚብስ የክፋት፣ የጭካኔና የጥፋት ስብዕና የተላበሱ ታህተ-ሰብዕ ሰዎች የሚሰሩት አሳፋሪ ሞያ ሆኗል፡፡

ምክንያታዊ ልዩነቶች እንኳን በመቀራረብና በመነጋገር፣ በውይይታና በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበት ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር ሰው ሁሉ በእኩልነትና በሰላም አብሮ እንዲኖር የሚታገለው አፍቃሬ ሰብኡ ሞያ ጋዜጠኝነት የሰው ልጅ ወዶ ባልሆነው ተፈጥሯዊ ልዩነቱ ምክንያት እርስ በእርሱ እንዲጠፋፋ የሃሰት መረጃን የሚያሰራጭ ፀረ ሰው ሞያ ሆኖ ታይቷል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በሀገራችን እየተከሰቱ ባሉ ግጭቶች እንደምንታዘበው ሁልጊዜ እውነትን መሰረት አድርጎ ለሰው ልጆች ሕይወትና ደህንነት ዘብ የሚቆመው ታላቁ ሞያ ጋዜጠኝነት በሃሰተኛ መረጃ ስርጭትና ቅስቀሳ ክቡር የሆነው የሰው ልጆች ሕይወት እንዲጠፋ ምክንያት ሲሆን ብሎም ግጭቶች ወደ አስከፊው የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲለወጡ ሁነቶችን በልዩ ትኩረት ሲያስተላልፍ ሰምተናል፣ ተመልክተናል፡፡

ታዲያ ታላቁንና ክቡሩን ሞያ በዚህ መንገድ የሚተገብሩ ሰዎችን ስናይ "እነዚህ ሰዎች እንዲህ የሚያደርጉት እውነት የሞያውን ምንነት፣ ሥነ ምግባርና ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ሕይወት የሚያበረክተውን ታላቅ አስተዋጽኦ ያህል በአግባቡ ካልተገበሩት በዚያው ልክ የሚያስከትለውን ታላቅ ጥፋት የማያውቁት ሆነው ይሆን?" "ወይስ እያወቁትም ቢሆን እንዲያደርጉት የሚያስገድድ ከፉ አለቃ ኖሮባቸው ይሆን?" ብለን መጠየቃችን የማይቀር ነው፡፡

**ጥፋቱ የሚፈጸመው በሰው ልጆች ሕይወትና በሕዝብ ላይ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ያማል፡፡ እናም "ሰው አየ፣ እግዚአብሔር አየ" ነውና፣ የሕሊና ሰላም ባለበት ደረቅ ቆሎ፤ በክህደት ከሚቆረጥ ጮማ ይበልጣልና በእንዲህ ዓይነት አጥፊ የጋዜጠኝነት ተግባር ላይ የተሰማራችሁ ወገኖች ለገንዘብ ወይንም ለቁሳዊ ጥቅም ከሆነ በዚህ የጥፋት ድርጊት ላይ የተሰማሩት ቢተውት መልካም ነው**

እኔ ሁለተኛው ነው የሚል ጥርጣሬ አለኝ - እያወቁትም ቢሆን በግዴታ ከእውነታው የሚያጣላ፣ ሕሊናቸውን አውሮ፣ እጅና እግራቸውን አስሮ ለጥፋት የሚያሰማራ አደገኛ አለቃ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ የአለቃው ስምም "አዛዥ ጥቅሙ" ይባላል (የኔ ግምት ነው እንግዲህ)፡፡ አለቃው በጠባብ የጥቅም ፖለቲካ ሕዝብን በተለያዩ መንገድ በመከፋፈልና በመነጣጠል ከዚያም እንደ ግል ቤቱ በብቸኝነት አጥሮ ይዞ፣ ሕዝብን በማስያዣነት አቅርቦ የስልጣንም ሆነ የገንዘብ ጥሙን ለማርካትና የፈለገውን ሁሉ ማግኘት ነው

ሕሊና የመልካምና ክፉ ነገሮች ሁሉ መመዘኛ፣ የእውነተኛው ዳኛ መቀመጫ መንበረ እግዚአብሔር ነውና ለጥቅም ብሎ አንድን ጥፋት ሆን ብሎ እያወቁ መፈጸም የኋላ ኋላ እረፍት አይሰጥም፡፡ ጥፋቱ የሚፈጸመው በሰው ልጆች ሕይወትና በሕዝብ ላይ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ያማል፡፡ እናም "ሰው አየ፣ እግዚአብሔር አየ" ነውና፣ የሕሊና ሰላም ባለበት ደረቅ ቆሎ፤ በክህደት ከሚቆረጥ ጮማ ይበልጣልና በእንዲህ ዓይነት አጥፊ የጋዜጠኝነት ተግባር ላይ የተሰማራችሁ ወገኖች ለገንዘብ ወይንም ለቁሳዊ ጥቅም ከሆነ በዚህ የጥፋት ድርጊት ላይ የተሰማሩት ቢተውት መልካም ነው፡፡

ሁለተኛ ነገር በሕዝብ ላይ የሚሰራ በደል ከበደል ሁሉ የከፋ ነው፡፡ የተማሩ መሃይማን ሊያፈርሷት የሚታገሏትን አገር ሳይማር በጥበብ ገንብቶ ታላቅ አገር ለትውልድ ያወረሰ ታላቅ ሕዝብን በገንዘብ፣ በቁሳዊ ጥቅም አለያም በርካሽ ፖለቲካዊ ፍላጎትና ስልጣን ጥማት የደህንነት መንገድ የሆነውን መልካሙን ሞያ ተጠቅሞ ሕዝብ ላይ ለጥፋት መዝመት አንድ ቀን በራስ ላይ ጥፋት ያመጣል፡፡

ሚዲያን ተጠቅመው የሩዋንዳን ሕዝብ ለጥፋት የዳረጉት የጥፋት አበጋዞች እነርሱም አልተረፉም፤ በደገሱት የጥፋት ማዕበል አብረው ጠፍተዋል፡፡ ይህን የምለው እነዚህ የጥፋት ተዋንያን በምክር ይመለሳሉ ብየ አይደለም፡፡ በሌላው መንገድ ሞክረውት፣ ሞክረውት አልሳካ ያላቸው እና ሚዲያንና ክቡር የሆነውን ሞያ በመጠቀም አሁን ላይ ሕዝብን በሕዝብ እያነሳሱ በሃገር ላይ ጥፋትን እየደገሱ የሚገኙት እንዲህ ዓይነቶቹ የጥፋት ልጆች አብዛኞቹ ፍቅርና ይቅርታ አያውቁም፡፡

ይቅርታ ስታደርግላቸው የሚገድሉ፣ ስትስማቸው የሚነክሱ እነዚህ የጥፋት ልጆች ለየት ያሉ ፍጡራን በመሆናቸው እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ እነርሱ ጋር አይሰራም፡፡ እናም ከተለመደው አካሄድ የተለየ ለእነርሱ ባህርይ የሚሆን ተገቢነት ያለው ተጨባጭ እውነታውን የሚዋጅ የመፍትሔ እርምጃ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ማለትም ለጥቅሙ ሲል ወድዶ ሕሊናውን ሽጦ በጥፋት ተግባር ላይ ለሚሰማራ ኃይል ለክቡሩ የሰው ልጅ ሕይወት ደህንነት ሲባል በሕግ ተገድዶ ከጥፋቱ እንዲመለስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ክቡር ለሆነው የሰው ልጅ የሚያገለግለው ክቡሩ ሞያ ጋዜጠኝነት በክብር ይያዝ፤ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# የጥራት መንደር- ለላቀ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት

**በኃይሉ አበራ**



ጥራት ለአንድ ሃገር የወጪ ምርት ተወዳዳሪነት ለገቢ ምርት ደህንነትና ወሳኝ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ አይሶ ያሉ ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተቋማት ተቋ ቁመው ይሰራሉ፡፡ አንደ ሀገርም የጥራት አረጋጋጭ ተቋማት ተቋቁመው ይሰራሉ፡፡

የጥራት ማረጋገጫ ደረጃዎች ቴክኖሎጂና ሳይንስን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ያገናዘቡ እና ከሌሎች የዓለም ሃገራት አንፃር የተናበቡ መሆን ይኖርባቸዋል። የሀገር ውስጥ ምርትም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እና ለማኅበረሰብ ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጡ ከሆነ በአምራቹና ላኪው ብሎም በምርቱ ተጠቃሚ ዘንድ ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡

ባለሀብቱም ላለመክሰር ሲል ጥራት ያለውን ምርት ለገበያ ማቅረብ ይፈልጋል። ማኅበረሰቡም ጥራታቸውን ያልጠበቁ ምርቶች በመጠቀም ከሚመጣበት የጤና እና የተለያዩ ችግሮች ለመዳን ጥራት ያለው ምርት ማግኘት ይመርጣል።

ሃገራት በየጊዜው የጥራት መስፈርቶቻቸውንና ደረጃዎች እያሻሻሉ ተግባራዊ ሲያደርጉ ይስተዋላል። ኢትዮጵያም በጥራት ላይ የሚሰሩ ተቋማትን አቋቁማ ስትሰራ ቆይታለች፡፡ በቅርቡ ደግሞ አዲስ የጥራት መንደር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት ይፋ አድርጋለች፡፡

በዚሁ መድረክ ላይ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዶክተር ካሳሁን ጎፌ እንደገለጹት፤ የጥራት መንደሩ በሰባት ነጥብ 2 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ 20 ሕንፃዎችን ያካተተ ነው። አጠቃላይ ወደ ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ እንደተናገሩት፤ የዚህ የጥራት መንደር ስያሜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት የሚባል ሲሆን፣ መሰረተ ልማት ብቻ ሳይሆን የጥራት መሰረተ ልማት ነው። በዚህ የጥራት መንደር ውስጥ በሺ የሚቆጠሩ ወጣት ሙያተኞች ይሰራሉ። በተለይም ምግቦችን፣ አልባሳትን፣ ኮንስትራክሽንን ግብአቶች የሆኑትን ሲሚንቶ፣ ብረት፣ መስታወት፣ ቆርቆሮ፣ እንዲሁም ከጤና ጋር የሚያያዙ መሳሪያዎችን ጨምሮ ይጠግናሉ፤ ጥራታቸውም ይፈተሻሉ።

ቡናው፣ ሰሊጡ፣ ማሩ ሁሉንም ዓይነት ምግብ ነክ ነገር ወደ ውጭ የሚላክ በሙሉ በዚህ ተቋም ተመዝኖ ዓለም አቀፍ ደረጃ መሆኑ ይረጋገጣል። ከውጭ የሚገቡም እንዲሁ ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ ከመውጣታቸው በፊት በጥራት መንደሩ ይፈተሻሉ። አልባሳት፣ ምግብ እና ጤና ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። በትናንሽ ንክኪዎች፣ ኬሚካሎች ምክንያት የጤና መጓደል ሊያጋጥም ይችላል፤ እናም ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡

ይህ መሰረተ ልማት በኢትዮጵያ ትልቅ ሲሳይ ሲሆን፣ በአፍሪካ ደረጃም እንዲህ አይነቱ መሰረተ ልማት ያላቸው ጥቂት ሃገራት ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የጥራት መሠረተ ልማት የሌላቸው ሀገራት ዘላቂ ዕድገት ማረጋገጥ እንደማይችሉም አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የዕድገት መሠረቱ የኤክስፖርት አቅም ነው። ሀገራት ኤክስፖርት ለማድረግ እንደዚህ ዓይነት ተቋም በእጅጉ ያስፈልጓቸዋል። መከላከያን፣ ፖሊስን ወይም ሰፋፊ መንገዶችን ከመገንባት በላይ አስፈላጊ ተቋም ነው። ይህ ተቋም በተሟላ አቅም ሲሰራ ወጪ ንግዱ ያድጋል፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትም በጥራት የተመረቱ ይሆናሉ። ሃገሪቱም በዓለም ገበያ የሚመረቱ ጥራት የጎደላቸው ምርቶች የሚጣሉባት አትሆንም ሲሉ ጠቅሰው፣ ተቋሙ ምርጥ ምርጡን የምትቀበል፣ በጥራት አምርታ የምትልክ ሀገር እንደሚያደርጋት አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስረዱት፤ በመጀመሪያ ተሞክሮው የተወሰደው ከደቡብ አፍሪካ ሲሆን፣ ደቡብ አፍሪካ ሲ.ኤስ.አር ከሚባል የጥራት መሰረተ ልማት ተቋም አላት። ከዚሁ ከ30 ያላነሱ ዓመታት ተሞክሮ ካለው የደቡብ አፍሪካ ተቋም ልምድ በመቀመር ኢትዮጵያም መሰል ተቋም እንዲኖራት ብዙ የተደከመበት ሥራ ነው። አሁን ፍሬያማ ሆኖ መሳሪያዎቹ ገብተው፣ ሙያተኞቹ ሰልጥነው በተሟላ ሁኔታ የኢትዮጵያን የወጪ ገቢ ንግድ ተወዳዳሪ ማድረግ የሚችሉ አቅሞች የሚፈጥር ነው። የትኛዎቹም በውጭ አገር ያሉ መሰል ስራ የሚሰሩ ተቋማት ቢመጡ የእነዚህን ላቦራቶሪ ደረጃ ስለሚያውቁት በትክክል ለመገልገልም ፍቃደኛ ይሆናሉ።

ከሃገር ውስጥ በዚህ ቦታ የጥራት ሰርተፊኬት አግኝተው የወጡ ምርቶች በቀላሉ በዓለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነት ይኖራቸዋል ሲሉም ጠቅሰው፣ እንደነዚህ ዓይነት ተቋማት መስከረም ተተክለው ጥቅምት የሚመረቁ ሳይሆን ሶስት እና አራት ዓመታትን ይጠይቃሉ፤ መዘጋጀትና ግብዓት ማግኘት ይፈልጋል ብለዋል።

በግቢው ከ20 በላይ ሕንፃዎች ያሉ ሲሆን፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ውጤት ከተገኘባቸው ተቋማት አንዱ ነው። ይህ ከገነባናቸው ሃገራዊ ተቋማት መካከል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ በጣም ጠቃሚ ተቋም ነው ሲሉም አስታውቀዋል፡፡

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርሀተስፋ የምጣኔ ሀብት አማካሪ ናቸው፡፡ በተባበሩት መንግስታት ኒውዮርክ የፖሊሲ አማካሪ ሆነው ያገለገሉና አሁን በሰብአዊ ድርጅቶች አመራር ላይ በመምህርነት እያገለገሉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባቸው የፋብሪካ ምርቶች በማኅበረሰቡ ላይ የጤናም ሆነ ሌሎች ችግሮችን ከማስከተላቸው በፊት ጥራታቸው በተገቢው መንገድ ተፈትሾ መግባት እንዳለባቸው ያመለክታሉ።

‹‹በመጀመሪያ ደረጃ አገራችን ከውጭ የምታስገባቸው ሁሉም እቃዎች፣ መድሃኒቶች፣ የኤሌክትሮኒክስ ቁሶች፣ ምግብ ነክ ነገሮች፣ አልባሳት ጭምር ጥራታቸው ታውቆና ተገምግሞ መግባት ይኖርባቸዋል›› ይላሉ። በመሆኑም የጥራት መንደር ምስረታው ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይጠቅሳሉ፡፡

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ በሃገሪቱ የጥራት ጥያቄዎች ምላሽ የሆነው የጥራት መንደር ምስረታው በየዘርፉ ከጥራት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የማኅበረሰብ ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የጥራት መንደር ምስረታው መንግስት ሃገርና የሕዝቡን ደህንነት ከመጠበቅ ሌላ የቁጥጥር ስራ አንዱ ነው፡፡

የጥራት መጠበቂያ ቦታዎች መዘጋጀታቸው ለወጪ ንግዱም ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰቡ ለሚጠቀምባቸው ነገሮች ደረጃዎች እያወጡ እርማት በማድረግ ማኅበረሰቡንም ሊመርዙ የሚችሉ ነገሮች ወደ ገበያ እንዳይቀርቡ ቁጥጥር ማድረግ ያስችላል የሚል እምነት አላቸው።

ላቦራቶሪያቸውን ብቻ መያዝ ሳይሆን ከገበያ ናሙና እየወሰዱ ምርምር ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታም ይፈጠራል። ይህም ለመንግስት አቅም ግንባታ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ማንኛውም በፋብሪካዎች የተመረተ እቃ የ'ISO' የዓለም አቀፍ ጥራት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ወደ ውጭ የሚላኩበት ሁኔታን ይፈጥራል።

የአውሮፓም ሆነ የሌላ ሃገራት መንግስታት ወደ ውጭ የሚልኩ ኩባንያዎች፣ የሚጠይቋቸው መስፈርቶች መኖራቸውን አስታውሰው፤ መስፈርቶቹ ከአካባቢ፣ ከኬሚካል ይዘት እንዲሁም ከሕፃናት በሥራ መሳተፍ ጋር የተያያዙ መሆናቸውንም ያመለክታሉ። ‹‹ እኛ በአብዛኛው ከ70 በመቶ በላይ ወደ ውጭ የምንልካቸው እቃዎች በጥሬ ነው። ቡናም፣ በሰሊጥም ሌሎችም አዝዕርቶችን ጨምሮ እሴት ተጨምሮባቸው ወደውጭ ቢላኩ ኢኮኖሚውን በተሻለ የሚደግፍ ይሆናል›› ሲሉም አስታውቀዋል።

ሰሊጥ ወደ ዘይት ተቀይሮ ወደ ውጭ ቢላክ በብዙ እጥፍ ዋጋው እንደሚጨምር ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ይጠቅሳሉ፡፡ በተጨማሪም ከውጭ የሚመጣውንም ዘይት በማስቀረት የውጭ ምንዛሬን መታደግ እንደሚያስችል ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም የጥራት መንደር መመስረቱ ይህንን እውን ለማድረግ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ገልጸዋል፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን እሴት ተጨምሮባቸው ወደ ወጭ ሊወጡ የሚችሉ እቃዎችን ለማምረት የሚያስችሉ ናቸው። እነዚህ ኩባንያዎች በተለይ ነፃ ኢኮኖሚ ዞን በሚባሉት አካባቢዎች ሲሰሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ሰርተው ወደ ውጭ እንዲልኩ ነው። ከመንግስትም በርካታ እድሎች ይሰጣቸዋል። ፈቃድ ለማውጣት መጉላላት ጋር በተያያዘ ብዙ ጥቅም አላቸው። እነዚህ የኢኮኖሚክ ዞን የሚባሉትና እነ ቻይና፣ ዩናይትድ አረብ ኢምሬት፣ ሲንጋፖር የመሳሰሉት በከፍተኛ ደረጃ ያደጉባቸው ስለሆኑ በአንድ በኩል ተጀምሯል፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በሙሉ ወደዚያ ለመቀየር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ያብራራሉ።

እምሩ አያሌው ኢምፖርት ኤክስፖርት የተሰኘ የግል ኩባንያ መስራችና ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ እምሩ አያሌው ጥራት የሁሉም ነገር ምንጭ ነው ይላሉ። አኩሪ አተር፣ ሰሊጥ፣ ኑግ የመሳሰሉትን ወደ ውጪ የሚልኩ ሲሆን፣ መኪና እና ማሽነሪዎችን ጎማዎችን፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃዎችን እንዲሁም ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሉ።

የጥራት መንደር ምስረታው የአስመጪና ላኪውም ንግድ ስራ የተሻለ የተሳለጠ የሚያደርግ መሆኑን አቶ እምሩ ጠቅሰው፣ ጥራት የሌላቸው እቃዎች በሚላኩበት ጊዜ ደንበኛን ማጣት ይኖራል ሲሉ ይገልጻሉ። የሚወስደውም ሰው ሸያጩን ሙሉለሙሉ ሰርዞ ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ እንደሚችል ተናግረው፣ ጥራትን ማዕከል አድርጎ የጥራት መንደሩ መሰራቱ ለአገርም ለነጋዴውም ወሳኝ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

ቀደም ሲል ወደ ውጭ ለመላክ የምናቀርባቸው የጥራት ሰርተፊኬቶች ነበሩ፤ ወደ አገር ውስጥ ስናስገባም ጥራትን መሰረት ያደረጉ ግምገማዎች ይደረጋሉ ሲሉ አመልክተው፣ ያንን ያህል ጠንካራ እና ኣመኔታ ግን የነበራቸው አይደሉም ብለዋል። በግለሰብ ደረጃ የሚሰሩ ጥራትን እናረጋግጣለን የሚሉ ተቋማት እንደነበሩ አስታውሰው፣ እነዚህ ተቋማት በቀላል ነገር በመግባባት ሰርተፊኬቱን ሊሰሩ የሚችሉበት እድል የሰፋ መሆኑን ነው የገለጹት።

የዚህ የጥራት መንደር ምስረታ የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዳለው ጠቅሰው፣ በመንግስት ቁጥጥር ስር ስለሆነ ጥራት የሌለውን እቃ ጥራት እንዳለው አስመስሎ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የማቅረቡ ሁኔታ አይታሰብም ሲሉ ተናግረዋል።

የጥራት መንደሩ እውን መሆኑ ጥራት ያለው እቃ ወደ ውጭ እንዲወጣ፤ ጥራት ያለው እቃም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ምቹ እንደሚፈጥር አስታውቀው፣ የጥራት መንደሩ የተሻለ ቴክኖሎጂ መጠቀሙ በውጭ ደንበኞች ዘንድ የተሻለ እምነት እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።

እኛ ለምንልከው እቃ ይበልጥ አመኔታን ይፈጥራል። ደንበኞች ጥራቱን የጠበቀ እቃ እንደሚደርሳቸው እርግጠኛ በሆኑ ጊዜ የተሻለ ክፍያ ይሰጣሉ ሲሉም አስታውቀው፣ አንዳንዴም ተጨማሪ ክፍያ ማግኘት ያስችላል ብለዋል።

የሚሸጠው እቃ ጥራት ሳይኖረው ቀርቶ ተጨማሪ ክፍያም ተቀብሎ ከተገኘ በቀጣይ ጥቁር መዝገብ ውስጥ ሊያስገባ እንደሚችል አመልክተው፣ የጥራት መንደሩ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ የሚያደርግ እንዲሁም የተሻለ የሰው ሀብት ተመድቦ የሚመራው ከሆነ የጥራት ጉዳይ በእጅጉ እንደሚሻሻል ገልጸዋል፡፡ ቴክኖሎጂዎቹ አገርንም አስመጪውንና ላኪውንም እንደሚያገለግሉ ጠቅሰው.፣ ቴክኖሎጂውን የሚመራ ባለሙያ በቦታው ማስቀመጥ ተገቢ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ቲክቶክ እና ንባብ

**ዋሲሁን ደበበ**

በፈረንጆቹ ጥር 1 ቀን 2024 (ከ11 ወራት በፊት ማለት ነው) በ‹‹ሬድ ፌም›› ድረ ገጽ ላይ የተሰነደ አንድ የጥናት ጽሑፍ ‹‹የታዳጊዎች የንባብ ባህል እና ማህበራዊ ሚዲያ›› ይላል:: ወደ ዝርዝር ይዘቱ ስንገባ፤ እንደ ቲክቶክ ያሉ የማህበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች የታዳጊዎችን የንባብ ባህል የሚያቀጭጩ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው:: በመቶኛ ሲሰላ፤ በሚታዩ ነገሮች (ቲክቶክ) ላይ ያለው የልጆች ዝንባሌ የበዛ መሆኑን ይገልጻል::

ይህን ለማወቅ ጥናት እንደማያስፈልገው አምናለሁ:: ትኩረቴን የሳበው ግን ጥናቱ የተሠራው አውሮፓ ውስጥ ባሉ ሀገራት መሆኑ ነው:: በዩክሬን ኪዬቭ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት፣ ኮምኒኬሽን እና አርትዖት ትምህርት ክፍል የተደረገው ይህ የዳሰሳ ጥናት፤ እንደ ቲክቶክ እና ኢንስታግራም ያሉ የማህበራዊ ገጾች ለንባብ ባህል አደገኛ መሆናቸውን ይገልጻል::

ልብ በሉ እንግዲህ! ይህ ጥናት የተደረገው የንባብ ልምዳቸው የዳበረ ነው በሚባሉት ሀገራት ነው:: ፈታኝነቱ እዚያ ድረስ ሆኗል ማለት ነው:: እዚህ ላይ ግን ልብ ማለት ያለብን ነገር፤ ስጋቱ የተገለጸው በታዳጊዎች ላይ ነው:: አዋቂዎች የተሻለ የመረዳት አቅም ስላላቸው ራሳቸውን ችለው ይወስናሉ ተብሎ ነው::

ወደ እኛ ሀገር እንምጣ:: ጥናቱ በኢትዮጵያ ይደረግ ቢባል፤ አደገኛ የሚሆነው ከልጆች ይልቅ አዋቂዎች ላይ ይሆናል:: ምክንያቱም ከልጆች በላይ አዋቂዎች ከንባብ ውጭ እየሆኑ ነው:: ከልጆች በላይ ቲክቶክ ላይ ረጅም ጊዜ የሚያሳልፉት አዋቂዎች ናቸው::

አዋቂዎች ማንበብ፣ ሀገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ መመራመርና መሳተፍ ሲገባቸው፤ እንደ ቲክቶክ ያሉ የመጫወቻ ፕላትፎርሞች ላይ ካዘወተሩ፤ ንባብ የሚባል ነገር አይኖርም ማለት ነው::

ለመሆኑ ቲክቶክ በተለየ ሁኔታ ለንባብ ባህል መዳከም ምክንያት የሚሆነው ለምንድነው? ሊባል ይችላል:: ለምሳሌ፤ ፌስቡክ ትንሽም ቢሆን ለንባብ ባህል በጎ አስተዋፅኦ አለው:: ምንም እንኳን ነገሮችን በጥልቀትና በስፋት ለማየትና ለመመርመር የሚያስችል ባይሆንም፤ ቢያንስ ከ1000 በላይ የሚሆን ቃላት ያላቸው ጽሑፎች ይነበቡበታል:: ቲክቶክ ግን የቪዲዮ ነው:: የሚታዩት ነገሮች በጣም አጫጭር መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የሚነበቡ አይደሉም፤ የሚታዩ ብቻ ናቸው:: የቲክቶክን በጎ አስተዋፅኦ (ለምሳሌ ሙያዊ ነገሮችን በማስተዋወቅ) ከሳምንት በፊት በነበረን ጽሑፍ አይተናል:: ዛሬ ግን ለንባብ ያለውን አሉታዊ ሚና ብቻ ነው የምናየው::

ቲክቶክ በባህሪው አጫጭር ነገሮች ይበዙበታል:: በዚያ ላይ አብዛኞቹ ቀልድና ጨዋታዎች ናቸው:: እያሳሳቁ ይዘው የሚሄዱ ናቸው:: ረዘም ያለ ነገር ቢገኝ እንኳን፤ ቆም ብሎ ለመከታተል ዕድል አይሰጥም:: ‹‹ከዚህኛው ቀጥሎ ሌላ የተሻለ ነገር አገኛለሁ›› የሚል ስስት ቀልብ ይፈጥራል:: እያየነው ያለውን ነገር በደንብ እያብሰለሰሉ በጥልቀት ከመከታተል ይልቅ፤ ቀጥሎ ያለው ሊበልጥ ይችላል የሚል ጉጉት ይፈጥራል፤ ቀጥሎ ያለውን ለማየት ቶሎ ‹‹ስክሮል›› የማድረግ ስሜት ይፈጥራል:: ስለዚህ ረዘም ያለ ነገር ቢጫንበት እንኳን፤ ታግሶ እና ተረጋግቶ ለማየት የሚያስችል ሥነ ልቦና አይኖርም ማለት ነው፤ በባህሪው ጥልቀት ላላቸው ነገሮች ምቹ አይደለም::

ይሄ ነገር በኢትዮጵያ ደካማ የንባብ ባህል ላይ ሲጨመር አስቡት! በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆናል ማለት ነው:: በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ የንባብ ባህል ደካማ ነው ሲባል፤ ብዙ መጽሐፍ አናነብም ለማለት ብቻ ይመስላል፤ አስገራሚው ነገር ግን ሌላ ነው:: የንባብ ባህል የለንም ሲባል፤ ባለ ዲግሪ እና ባለ ማስተርስ ሆነው ጭራሹንም ማንበብ የማይችሉ አሉ ለማለት ጭምር ነው:: ይሄ ማለት ልክ በደርግ ዘመነ መንግሥት መሠረተ ትምህርት ይማሩ የነበሩ እናቶቻችን እየተንቀጠቀጡ እና የሆሄያቱን ስም ለየብቻ እየጠሩ የሚያነቡ አሉ ማለት ነው:: ሲያነቡ፤ እያንዳንዱን ቃል እንደገና እየደገሙ የሚጠሩ አሉ ማለት ነው:: ስለዚህ የምናወራው ስለንባብ ባህል መዳበር ብቻ ሳይሆን፤ አነባበብ የመለማመድ ጉዳይ ላይ ጭምር ነው::

‹‹እንዴት ይሄ ሊሆን ይችላል?›› ብሎ የሚገረም ሊኖር ይችላል:: እንደሚታወቀው የትምህርት ሥርዓታችን ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ በእንግሊዝኛ ነው:: ብዙ የገጠር ልጆች ደግሞ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ፤ ከመማሪያ መጻሕፍት ውጭ አያነቡም:: እነዚህ ልጆች እንደዚሁ እንደሆኑ ዩኒቨርሲቲ ይገባሉ:: ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚማሩትም በእንግሊዝኛ ስለሆነ ቆይታቸው ከሀገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች የራቀ ነው:: እንደዚሁ እንደሆኑ ሥራ ይቀጠራሉ::

የሥራቸው ባህሪ ከኮምፒተር ጋር የሆነ ባለሙያዎች አሁንም ከንባብ እንደራቁ ናቸው ማለት ነው:: በኮምፒተር የሚጠቀሟቸው ነገሮች ሁሉ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው:: የቀን እና የሰዓት አቆጣጠሩ ሁሉ ሳይቀር በአውሮፓውያኑ ነው:: ትምህርቱም፣ ሥራውም ሀገራዊ ጉዳዮችን በሀገርኛ ቋንቋ እንዲያነቡ አያደርግም:: ይህን ሁሉ አጥር ጥሰው የሚወጡት ጥቂቶች ናቸው::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፌስቡክ ሲመጣ ትንሽም ቢሆን በሀገር ውስጥ ቋንቋ (በተለይም በአማርኛ) የሚጻፉ ነገሮችን ማንበብ አስቻለ:: በፌስቡክ ብቻ ንባብ የተለማመዱ አሉ ማለት ይቻላል:: እነዚህ ሰዎች በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ሆነው፤ ባለ ዲግሪ ሆነው፣ አማርኛ ማንበብ የማይችሉ ይሆኑ ነበር ማለት ነው::

ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች ንባብ ሳይለማመድ ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ወጣት ቲክቶክ ላይ ሲጣድ የሚያጋጥመውን አስቡት:: በአማርኛ ቋንቋ ጭራሹንም ማንበብ የማይችል ሊሆን ይችላል ማለት ነው:: ለሀገራዊ ጉዳዮች ሩቅ ይሆናል ማለት ነው:: ሀገራዊ ጉዳዮች ደግሞ በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች እንጂ በእንግሊዝኛ ብዙም አልተጻፉም:: ወግና ባህሎቻችን በራሳችን ቋንቋዎች እንጂ በእንግሊዝኛ ተጽፈው የልብ አያደርሱም::

ቲክቶክ ላይ መማር፣ ሀገራዊ ጉዳዮችን መከታተልና ማወቅ አይቻልም ወይ? ሊባል ይችላል:: በጥልቀትና በስፋት ማወቅ አይቻልም:: ሽፋፋ እና የለብ ለብ ይሆናል:: ሳይንሳዊ ባህሪውንም ልብ እንበል፤ በንባብ ማወቅ እና በመስማትና በማየት ብቻ ማወቅ ይለያያሉ::

በንባብ ማወቅ የአስተሳሰብ አድማስን ያሰፋል:: ጥልቀት አለው:: እየሰሙ ወይም እያዩ ማለፍ ብቻ ሳይሆን፤ ቆም እያሉ የማሰብና የማሰላሰል ዕድል ይሰጣል:: አንድ ሰው ሲያነብ፤ ለራሱም ሃሳብ ይመጣለታል:: እየተረጎመውና እያብሰለሰለው ይሄዳል:: መረጃዎችን በሚገባ ወደ ውስጡ ያስገባቸዋል:: በዕይታ ሲሆን ግን የሚታየው ነገር ባተሌ ያደርገዋል:: በሚታየው ነገር ማራኪነት (ቀልብ ሳቢነት) የሚነገረውን መረጃ ልብ ላይለው ይችላል:: በቲክቶክ ሲሆን ደግሞ በባህሪው ቀልብን ‹‹ቢዚ›› ስለሚያደርግ ጠንካራ ጉዳዮችን ተረጋግቶ ለማየት አያስችልም፤ የሚያዩ ሊኖሩ ይችላሉ፤ አብዛኛውን ግን አይወክሉም::

እንግዲህ በዚህ ልማድ ውስጥ የሚያልፍ ትውልድ ተናጋሪ ብቻ እንጂ አሳቢ አይሆንም ማለት ነው:: በጥልቀት የማሰብና የመረጋጋት፣ አርቆ የማስተዋልና የማሰብ ባህሪ የሚዳብረው በንባብ ነው:: የሠለጠነ እና የበሰለ አዕምሮ መገንባት የሚቻለው በንባብ ነው:: አለበለዚያ ለፍላፊ እና ቀዥቃዣ ባህሪ ነው የሚፈጠረው::

ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ስማርት ስልክ የሚይዙ ልጆች ከንባብ ጋር ሳይተዋወቁ ያድጋሉ ማለት ነው:: ስለዚህ አዋቂዎች ልጆቻቸውን ቢመክሩ፤ ራሳቸውም ከቲክቶክ ቆጠብ ይበሉ::

# ዓለም አቀፍ

## በዩኒቨርሲቲው መጋዘን ውስጥ 350 ሺህ የአፍሪካ ቅርሶች ተገኙ

በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ መጋዘን ውስጥ 350ሺህ መሆናቸው የተገመተ የአፍሪካ ቅርሶች፣ የእጅ ጽሑፎች፣ የሰው ቅሪተ አካሎች፣ ፎቶግራፎች እና የተፈጥሮ ታሪክ ናሙናዎች ተገኙ። ዩኒቨርሲቲው ካከማቻቸው ስብስቦች ውስጥ ግብፅ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ አርኪዎሎጂያዊ ቅርሶች እና የእጅ ጽሑፎች ያላት አፍሪካዊ ሀገር ነች ተብሏል።



ኢቫ ናሙሶኬ (ዶ/ር )ከካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ቅርሳ ቅርሶቹን ለመለየት ከዩኒቨርሲቲው የቤተ-መጻሕፍት ሠራተኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ቤተ-መዛግብት አስተዳዳሪዎች እና ሰናጆች ጋር በመሆን በመጋዘናቸው ውስጥ ለ15 ወራት ማሳለፋቸው ተገልጿል። ትላልቅ ሙዚየሞች ያላቸውን ስብስቦች በሙሉ አለማሳየታቸው “በጣም የተለመደ ነው”፤ ነገር ግን “በዚህ መጠን እና ዓይነት ከመላው አፍሪካ አህጉር እንዲሁም አንዳንዶቹ ቅርሶች ለበርካታ አስርት ዓመታት ተቀምጠው መገኘታቸው አሁንም የሚያስገርም ነው” ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ ዩኒቨርሲቲው በቅርብ ጊዜ ሙዚየሙ ከቅኝ ግዛት እና ከባርነት ጋር ተያይዞ የሚነሱበትን ጥያቄዎች ለመቅረፍ የተጀመረ ሲሆን፣ እግረ መንገዱንም አብዛኞቹ ቅርሶች በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ወቅት የተገኙ መሆናቸውን አሳይቷል።

የፊትዝዊሊያም ሙዚየም ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት ናሙሶኬ (ዶ/ር)ከአፍሪካ ጋር የተያያዙ አብዛኞቹ ቅርሶች አሁንም ለሕዝብ ዕይታ አይቀርቡም። አሁን ግን በስፋት ለዕይታ እንደሚቀርቡ እና ጥናት እና ምርመር እንደሚሠራባቸው ባለሙያዋ ተስፋ አድርገዋል።

እነዚህ ቅርሳ ቅርሶች በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሚገኙት ስምንት ሙዚየሞች፣ በዕፅዋት ሙዚየም እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ቤተመጻሕፍት እና ስብስቦች እንዳሏቸው እምብዛም በማይታወቁ የዩኒቨርሲቲው ትምህርት ክፍሎች እና ተቋማት ውስጥ ነው የተገኙት።

በቅኝ ግዛት አስተዳዳሪ ከተበረከቱት የማሳይ ጎሳ አባላት የክንድ አንባሮች ጀምሮ፣ በቦር ጦርነት (1899-1902) በማጎሪያ ካምፕ ከተሰበሰቡ ትንንሽ አጥቢ እንስሳት፣ የመካከለኛው ዘመን የአይሁድ የእጅ ጽሑፎች ስብስብ እና የአፍሪካ ሕዝቦችን የሚያሳዩ የመጀመሪያ ፎቶግራፎች ከተገኙት መካከል መሆናቸው ተጠቅሷል።

አብዛኞቹ ቅርሶች የተወሰዱት በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ወቅት ነው፤ አንዳንዶቹ በስጦታ የተበረከቱ፣ የተገዙ፣ በቁፋሮ የተገኙ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ የተዘረፉ፣ የተወረሱ እና የተመዘበሩ ናቸው።

በዩኒቨርሲቲው አርኪዮሎጂ እና አንትሮፖሎጂ ሙዚየም ከጋና የመጣ የወርቅ ሀብል ያለ ሲሆን፣ በሦስተኛው የአንግሎ-አሳንቴ ጦርነት ወቅት፣ በአሳንቴሄኔ ኮፊ ካሪካሪ ቤተ መንግሥት በ1873-4 እንደተዘረፈ ይገመታል።

በተጨማሪም እንግሊዝ በ1897 በአሁኑ ደቡብ ናይጄሪያ በዚያን ጊዜው ቤኒን ሥርወ መንግሥት ለቅጣት በሚል በወሰደችው ርምጃ የተዘረፉ 116 እቃዎች ተገኝተዋል። ናሙሶኬ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ “በዓለም ዙሪያ ባሉ ብዙ ሙዚየሞች ውስጥ እንደሚታየው ሁሉ በዚህም እንደዚህ ዓይነት ቅርሶችን እንደማገኝ ጠብቄ ነበር” ብለዋል።

“ዩኒቨርሲቲው የዶዶ (እንስሳ) ቅሪተ አካልን ያገኘው በካምብሪጅ ውስጥ በሚገኝ አንድ ሰው እና በሞሪሺየስ ውስጥ ባለው የቅኝ ገዢ አስተዳዳሪ መካከል ባለው ግለሰባዊ ግንኙነት አማካኝነት ነው” ትላለች። “ከአንትሮፖሎጂ እና የቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ጋር ጥምረት አለ፤ ማለትም ተመራማሪዎች ሕዝቡን እና ባህሉን ለማጥናት እና ለመመርመር መግባባት አላቸው።”

ይህንንም በመጥቀስ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ይደረጉ የነበሩ ሳይንሳዊ ምርምሮችን ማድረግ እና መረጃ መሰብሰብ ከቅኝ ግዛት ጋር “እጅ ለእጅ ተያይዘው ይሄዱ ነበር” ትላለች። በዩኒቨርሲቲው ስብስቦች ውስጥ ግብፅ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ አርኪዮሎጂያዊ እቃዎች እና የእጅ ጽሑፎች ያላት አፍሪካዊ ሀገር ነች።

የዶ/ር ናሙሶኬ መረጃ እንደሚያሳየው አፍሪካውያን ናሙናዎችን ወይም ቅርሶችን ለመሰብሰብ ስላደረጉት አበርክቶ፣ ስላካፈሉት ክህሎት፣ ዕውቀት በጣም በሚያስቆጭ መልኩ “ጥቂት” ብቻ ተሰንዷል። “ከ1930ዎቹ ጀምሮ በካሜሩን ስለሆነው የምናገረው አንድ ምሳሌ አለ፤ ይህም ከፍተኛ መጠን ያለው የአፍሪካውያን አቅም የጉልበት ሥራ ላይ መዋሉ ግልጽ ነው” ስትል ተናግራለች።

ፕሮጀክቱ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ተነሳሽነት የሚሠራ ሲሆን፣ ያሉትን ቅርሳ ቅርሶች ከማኅበረሰቦች ጋር ለማስተሳሰር ያለመ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በተለይም ከአፍሪካ ምሁራን እና ማኅበረሰቦች ጋር ተጨማሪ ምርምርን፣ ትብብርን እና ተሳትፎን ለማስተዋወቅ አቅዷል። ዶክተር ናሙሶኬ። “የሚቀጥለው ትልቅ ርምጃ ግን ዕይታን መጨመር እና ስብስቦቹን ራሳቸው አፍሪካውያኑ እንዲመራመሩ መፍቀድ ነው” ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# የኢትዮጵያ አቪዬሽን ባለውለታ-ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ

ክብረአብ በላቸው

በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ባገኛቸው ዕድሎች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ዕውቀት ለመቅሰምና የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት የቻሉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ያገኙትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለማድረስና አዳዲስ እሠራርንና አስተሳሰብን ለማስረጽ፣ አብዝተው የደከሙና ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መስጠት የደረሱ ፋና ወጊ ግለሰቦች እንደ ነበሩ ይታወቃል።

ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸው ደኅንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መሥዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልበሩም። በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በእምነት አስተምሮ፣ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ናቸው።

ከእነዚህ የሀገር ባለውለታ ግለሰቦች መካከል ኢትዮጵያ በስፋት በምትታወቅበት የአቪየሽን ኢንደስትሪ ከባለሙያነት እስከ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ያገለገሉት የኢትዮጵያ አቪዬሽን ባለውለታ ካፕቴን ሙሐመድ አሕመድ አንዱ ናቸው።

የኢትዮጵያን ስም በመላው ዓለም በበጎ ከሚያስጠሩ ጥቂት ሀገር በቀል ተቋማት ውስጥ አንጋፋው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። ይህ የአፍሪካ ምልክት የሆነ ተቋም በተለያዩ ኢትዮጵያውያን እየተመራ እስከዛሬ ደርሷል። በአየር መንገዱ የረዥም ዘመን ጉዞ ውስጥ የራሳቸውን የላቀ አሻራ ካሳረፉ ግለሰቦች መካከል ካፕቴን ሙሐመድ አሕመድ ግንባር ቀደም ናቸው። በአቬዬሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከኢትዮጵያም አለፍ ሲል አፍሪካ ካየቻቸው ስመጥር የአየር መንገድ ሥራ አስፈፃሚዎች መካከል ካፕቴን ሙሐመድ አሕመድ ተጠቃሽ ናቸው።

በ1925 በሐረር የተወለዱት ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ፤ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙት አሜሪካን ሀገር ከሚገኘው ሴንት ሉዊስ ዩኒቨርሲቲ በኤሮናውቲካል ኢንጂነሪንግ ነው። በተመሣሣይ በዚያው ሀገር ስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲም ሥልጠና ወስደዋል።


ካፒቴን ሙሐመድ በሥራ ዓለም ቀድመው የተቀላቀሉት የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ነው። በተማሩበት ዘርፍ ግዙፉን የኢትዮጵያ አየር መንገድን የተቀላቀሉት ደግሞ ከ60 ዓመታት በፊት ነበር። በአየር መንገዱ ለ20 ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ከ1973 አንስቶ ከአስር ዓመታት በላይ አየር መንገዱን በዋና ሥራ አስፈጻሚነት መርተዋል።

ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ አትራፊ ሆኖ በቀጠለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ በሥራ አስኪያጅነት እስከ 1990 ድረስ በመስራት ከዚያም በሥራ ዕድገት ወደ አፍሪካ አቪዬሽን ወደ ናይሮቢ ተዛውረው ማገልገላቸውን ተገልጿል።

ካፒቴን ሙሐመድ የቀድሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በነበሩበት ወቅት አየር መንገዱን በታሪኩ እጅግ ፈታኝ ለውጥን በማሳለፍ ከ10 ዓመታት በላይ ያለፈ ስራ ሰርተዋል። ያበረከቱት አስተዋፅኦ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ወደ ላቀ ደረጃ ከማድረሱ ባለፈ በዓለም አቪዬሽን ኢንደስትሪ ላይ የማይረሳ አሻራ ጥሏል።

ካፒቴን ሙሐመድ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር የተቀላቀሉት የአውሮፕላን ዋና መሐንዲስ ሆነው ነበር። የአየር መንገዱን ቀደምት እድገት በመቅረጽ ረገድ የካፒቴን ሙሐመድ ቴክኒካዊ እውቀቱ እና የእይታ አስተሳሰብ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። እ.ኤ.አ. በ 1980 ወደ ዋና ሥራ አስፈፃሚነት ሲመጡ እጅግ ከባድ ኃላፊነት ነበር የጠበቃቸው።

በወቅቱ አየር መንገዱ በኢትዮጵያ የእርስ በርስ ጦርነት እና በደርግ መንግስት ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት ተደራራቢ ፈተናዎች አጋጥመውት ነበር። የካፒቴን ሙሐመድ አመራር በዚህን ወቅት አየር መንገዱን ለመታደግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። አየር መንገዱ ከፖለቲካ ተጽእኖ ነፃነቱን ለመጠበቅ የሰጡት ቁርጠኝነት የታከለበት ውሳኔ እስከዛሬ የአየር መንገዱን ሕልውና እና ዕድገት አረጋግጧል።



**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለአፍሪካ አቪዬሽን መብራት፤ ለአመራሩና ለራዕዩ ሕያው ምስጋና ሆኖ ዛሬ ቆሟል። በዚህ ሂደት የካፒቴን ሙሐመድ አስተዋጽኦ ጉልህ ነበር**

በእርሳቸው አመራርነት ዘመን ማለትም በ1980ዎቹ መጨረሻ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ መረጋጋትና ብልፅግና እንደተመለሰ የሰው ኃይል ማሻሻያዎችን እና ስልታዊ ሽርክናዎችን ጨምሮ የወሰዳቸው ወሳኝ ተግባራቶች አየር መንገዱን መልካም ስም ከመመለሳቸው ባሻገር ትርፋማ እንዲሆን አድርገውታል።

የካፒቴን ሙሐመድ ስኬት ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የተሻገረ ነው። እ.ኤ.አ. በ 1992 የአፍሪካ አየር መንገድ ማኅበር ዋና ፀሐፊ በመሆን የአፍሪካን አቪዬሽን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ እውቅና እንዲያገኝ አድርገዋል። እ.ኤ.አ. በ1990 ከካፒቴን ሙሐመድ ጋር የተገናኘው አሜሪካዊው ፀሃፊ ፖል ቢ. ሄንዜ፡- ካፕቴን ሙሐመድን በማደግ ላይ ከሚገኙ ሀገራት ውስጥ ከከፍተኛ ሥራ ፈጣሪዎች አንዱ፣ ለትውልድ ሀገራቸው እና ለእድገቷ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያላቸው መሪ እንደነበሩ ገልጿል።

ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ አየር መንገዱን በመሩበት ጊዜያት ከገባበት አጣብቂኝ እንዳወጡት የሕይወት ታሪካቸው መዛግብት ላይ ሠፍሮ ይገኛል።

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ አመራርነት በኋላ ያቀኑት ወደ አፍሪካ አየር መንገዶች ማኅበር ነው። ማኅበሩን ከ1985 አንስቶ መርተዋል። ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ በአቪየሽን ዘርፍ ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የዕውቅና ሽልማት በ1992 ተበርክቶላቸዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድን ተወዳዳሪ እና ምርጥ አየር መንገድ በማድረግ ረገድ የእኒህ ጉምቱ ባለሙያ ጥረት የሚዘነጋ አይደለም። የዓለማችን ዘመናዊ የንግድ አየር መንገድ በማድረግ መሰረት የጣሉ ከመጀመሪያ የአየር መንገዱ የመጀመሪያዎቹ ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ካፕቴን ሙሐመድ አሕመድ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

በተለይም ከ1963 በኃላ ዘመናዊና ትላልቅ አይሮፕላኖችን እንዲሁም ቦይንግ አይሮፕላን በማስገባት የበረራ መስመሩን አፍሪካና መካለኛው ምስራቅ በማድረግ በ1975 እስከ ቻይናና አውሮፖ ድረስ በረራ ያስጀመሩ ሥራ አስኪያጅ ናቸው።

ካፒቴን ሙሐመድ አየር መንገዱ በየግዜው የሚገጥመውን ፈተና በድል የተወጡ አመራር ናቸው። በተለይም ደርግ በሚከተለው ርዕዮተ ዓለም እሳቤ መሰረት አውሮፕላኖች መምጣት ያለባቸው ከሶሻሊስት ሀገራት ብቻ ነው የሚለውን ቀጭን ትዕዛዝ ባለመቀበል ደረጃቸውን የጠበቁ የቦይንግ ምርቶች ብቻ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደረጉ ቆራጥ አመራር ናቸው።

በዚህም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጥራታቸውን የጠበቁ አይሮፕላኖች ቦይንግ 727 እና 767 በማስመጣት ትልቅ ውለታ ለሀገራቸው አበርክተዋል።

በደርጉ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃ/ማሪያም ይህንን የአሜሪካን አይሮፕላን በሶቭየቶች አንቶኖቭ እንዲተካ ቢጠየቁ ካፕቴን ሙሐመድ በድርጅቱ አሰራር ጣልቃ እንዳይገቡ በማሳሰብ እና ለመንግስቱ ኃ/ማሪያም በማስረዳት አየር መንገዱን ጥራትና ዘመናዊ አይሮፕላን ተጠቃሚ በማድረግ የአየር መንገዱን ክብር ያስጠበቁ ባለሙያ ናቸው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለአሁኑ ስምና ዝናው ካበቁት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ የሆኑት ካፕቴን ሙሐመድ አሕመድ በሁለቱም ስርዓት ማለትም በንጉሳዊውና በደርግ ስርዓት አየር መንገዱን በዋና ሥራ አስኪያጅነት አስተዳድረዋል። በዚህም ወቅት አየር መንገዱ በዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ተፎካካሪ እንዲሆንና ዘመናዊነቱ ጠብቆ እንዲጓዝ በማድረግ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል ተብለው ይጠቀሳሉ።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ወይንም የኢትዮጵያን አየር መንገድ ወደ ዘመናዊና ተወዳዳሪ አየር መንገድ እንዲሸጋገር መሰረት ከጣሉት የመጀመሪያዎቹ ሥራ አስፈጻሚዎች ውስጥ ካፕቴን ሙሐመድ አሕመድ አንዱና በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ ሕይወት ፈተናን የመቋቋም፣ የፈጠራ እና የማይናወጥ የላቀ ቁርጠኝነት ማረጋገጫ ነበር። የእሳቸው ትሩፋት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ አሻራቸውን ለማሳረፍ የሚጥሩትን አፍሪካውያን ትውልዶችንም ማበረታታቱን ይቀጥላል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለአፍሪካ አቪዬሽን መብራት፣ ለአመራሩና ለራዕዩ ሕያው ምስጋና ሆኖ ዛሬ ቆሟል። በዚህ ሂደት የካፒቴን ሙሐመድ አስተዋጽኦ ጉልህ ነበር።

ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ ያበረከቱት አስተዋጾ ታላላቅ መሪዎች ተቋማትን በተግዳሮቶች ከመምራት ባለፈ ዘላቂ የሆኑ ትሩፋቶችን እንደሚተው ያስታውሰናል። በአየር መንገዱ የነበራቸው አስተዋጽኦ በኢትዮጵያ ታሪክ እና እሳቸውን የማወቅ እድል በነበራቸው ሁሉ ልብ ውስጥ ሲዘከር ይኖራል።

ካፕቴን ሙሐመድ፣ ሀገር በጭንቅ ሰዓት ስትጠራቸው የደረሱላት፣ አየር መንገዳችን በማዕበል ውስጥ ሲናጥ በቁርጠኝነት የመሩ፣ ኋላም ለትውልድ መሠረት ያለውን ተቋም በሶሻሊስት ሀገር ከካፒታሊስት ድርጅት ጋር ለመስራት የቻሉ፣ ጽኑ፣ የአየር መንገዳችን የቀድሞ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነበሩ።

በ92 ዓመታቸው ይህቺን ዓለም የተሰናበቱት ካፒቴን ሙሐመድ፣ በምስራቋ ፀሐይ ሐረር ተወልደው ያደጉ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ ነበሩ።

በኢትዮጵያ አየር መንገድ የ80 ዓመት ታሪክ፣ ወርቃማውን የአየር መንገዱን ታሪኮች በሥራቸው ከጻፉ መሪዎቹ በግንባር ቀደም የሚገኙት ካፒቴን ሙሐመድ፣ ከዚህ ዓለም ማለፉ የሰው ልጅ የመጨረሻው ዕጣ ፈንታ ቢሆንም፣ የደከሙለት አየር መንገድ ግን ሁሌም በስራ ላይ መሆኑን ማስታወስ የማንንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሕሊና ለላቀ እና የማያልፍ ስራ የሚያነሳሳ ሕያው ታሪክ ነው።

ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆነው ባገለገሉበት ወቅት አየር መንገዱ ዛሬ ለደረሰበት የስኬት ደረጃ እንዲበቃ መሰረት የጣሉ ውሳኔዎችን በማሳለፍ የማይተካ የመሪነት ሚናቸውን ተጫውተው አልፈዋል።

የካፒቴን ሙሐመድ አሕመድ ስርዐተ ቀብር ሕዳር 17 ቀን 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች፣ የቀድሞ የሥራ ባልደረቦቻቸው እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት በኮልፌ ሙስሊም መካነ መቃብር ተፈፅሟል።

እኛም በዚህ ለሕዝብና ለሀገራቸው መልካም ያደረጉና በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ የማይነጥፍ አሻራ ማኖር የቻሉ ግለሰቦች ታሪክ አንስተን ለአበረከቷቸው ክብር በምንሰጥበት በዚህ የባለውለታዎቻችን ዓምድ የቀድሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈጻሚና በአየር መንገዱ የዘመናት ስኬታማ ጉዞ የላቀ አበርክቶ የነበራቸውን ካፒቴን ሙሐመድ አሕመድን ላበረከቱት መልካም አሻራ አመሰገንን። ሰላም!

# ስፖርት





## በኦሊምፒክ ወርልድ ቴኳንዶ ለመሳተፍ ከወዲሁ ጥረት ይደረጋል

ዓለማየሁ ግዛው

ወርልድ ቴኳንዶ ከኦሊምፒክ ስፖርቶች አንዱና በርካታ ስፖርተኞች ለሜዳሊያ የሚፋለሙበት ነው። ሀገራትም ለዚህ ስፖርት ትልቅ ትኩረት ሠጥተው ይሠራሉ። ኢትዮጵያም ከውጤታማው አትሌቲክስ በተጨማሪ በቦክስ፣ ውሃ ዋና፣ ብስክሌት ስፖርቶች ባላት የኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ ላይ በ2020 ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ የወርልድ ቴኳንዶን አክላለች። ሰለሞን ቱፋ ደግሞ በዚህ ስፖርት ኢትዮጵያን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኦሊምፒክ የወከለ አትሌት እንደነበረ ይታወሳል። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ የወርልድ ቴኳንዶ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ባለፈው 2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ አልተደገመም።

ስፖርቱ በኢትዮጵያ በተለይም በወጣቱ ዘንድ ከፍተኛ ተዘውታሪነትና ተወዳጅነት ያለው ቢሆንም፣ በኦሊምፒክና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ውጤት ከማስመዝገብና ብዙ ተሳትፎ ከማድረግ አንጻር ብዙ ርቀት አልተጓዘም። ይህን በመቀየር ኢትዮጵያን ወደ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ለመመለስ በኦሊምፒክ ውድድር የሚደረግባቸው የተለያዩ ኪሎ ግራሞች ላይ መሠረት ያደረገ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን አሳውቋል።

ፌዴሬሽኑ ሰሞኑን ከደቡብ ኮርያ ኤምባሲ ጋር በመተባበር ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ የወርልድ ቴኳንዶ ስፖርተኞች የተሳተፉበት ለሁሉም ክፍት የሆነ ውድድር አከናውኗል። ውድድሩ የደቡብ ኮርያ አምባሳደር ስያሜን ይዞ "አምባሳደር ካፕ" በሚል ለአራተኛ ጊዜ ከኅዳር 20 እስከ 22/2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ነበር የተካሄደው።

በውድድሩ የተሳተፉ አትሌቶችም በብሔራዊ ቡድን ምርጫ ውስጥ መካተታቸው ታውቋል። የብሔራዊ ቡድን ምርጫው ኢትዮጵያን ወደ ኦሊምፒክ ውድድር ለመመለስና በአህጉር አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎና ውጤት ብቁ የሆነ ቡድን ለማዘጋጀት እንደሆነም ተገልጿል።



በውድድሩ የተሳተፉ ጠንካራ አትሌቶች በብሔራዊ ቡድን ይካተታሉ፣

የኢትዮጵያ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍቅሩ ተቋም፣ የዘንድሮው ውድድር በስፖርት ይዘትና ተሳትፎ አኳያ የሚለይ መሆኑን ይናገራሉ። አላማውም በሚያዝያ ወር ኢትዮጵያ ለምታዘጋጀው የአፍሪካ ፕሬዚዳንሻል ካፕ ብቃትና ችሎታ ያላቸውን ስፖርተኞች ለብሔራዊ ቡድን ለመምረጥ ነው። በኢትዮጵያ በሚካሄደው አህጉር አቀፍ ውድድር መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ሰሞኑን የተካሄደው ውድድር ጠንካራ ስፖርተኞችን ለመምረጥ እንዳስቻለ ኃላፊው ተናግረዋል።

ውድድሩ በተለያዩ የኪሎ ግራም ካታጎሪዎች ተከፍሎ የተካሄደ ሲሆን፣ በፍልሚያ (ስፓሪንግ) የኦሊምፒክ ኪሎዎችን ብቻ አካቶ ተካሂዷል። እነዚህም በወንድ 68 እና በሴት 58 ኪሎ ግራም፣ በሴት ከ 49 ኪሎ ግራም በታችና በወንድ ከ57 ኪሎ በታች መሆናቸው ታውቋል። በፑምሴ (አርት) የወጣቶች ከ16 እስከ 30 ዓመት፣ ከ16 ዓመት በታችና አዋቂዎች እንዲሁም ከ40 ዓመት በላይ የተካተቱበትም ነው።

ውድድሩ በየኪሎው ካታጎሪው ከአንድ ክልል አራት ስፖርተኛ እንዲሳተፍ እድል ተሰጥቶ በርካታ ጠንካራ ስፖርተኞች የተመለመሉበት መሆኑንም አቶ ፍቅሩ ይናገራሉ። የኦሊምፒክ መወዳደሪያ የተለያዩ ኪሎ ግራሞች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ከሆነ በቀጣይ ኦሊምፒክ ለመሳተፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራልም ይላሉ። ቴኳንዶ የንኪኪ ስፖርት በመሆኑና ሥልጠና እና ውድድሮች ላይ ጉዳቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ተጠባባቂዎችን ጨምሮ በየኪሎ ካታጎሪው አምስት አትሌቶች እንደሚመረጡም ጠቁመዋል።

ፌዴሬሽኑ በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ በወርልድ ቴኳንዶ ለመሳተፍ አቅዶ ዝግጅቶችን ቢጀምርም በቂ ጊዜ ሰጥቶ ዝግጅት ባለማድረጉ መሳተፍ እንዳልተቻለ የሚያስታውሱት አቶ ፍቅሩ፣ ከዚያ ትምህርት ተወስዶ በ2028ቱ የሎሳንጀለስ ኦሊምፒክ ለመሳተፍ ቀድሞ ዝግጅት መደረግ እንደሚኖርበት በፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ መወሰኑን ይገልጻሉ። ሰሞኑን እንደተካሄደው አይነት ውድድሮች ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቶችን በብዛት እንዲሳተፉና እንዲመረጡ የተፈለገውም ይህ ጉዳይ ከግንዛቤ ገብቶ ነው ይላሉ።

አቶ ፍቅሩ ከአራት ዓመት ያነሰ ጊዜ ለሚቀረው የኦሊምፒክ ውድድር ቀድሞ ትኩረት ተሰጥቶ ጥሩ ዝግጅት የሚደረግ ከሆነ በቀላሉ መሳተፍ ይቻላል ባይ ናቸው። በሰሞኑ ውድድር የተመረጡ ስፖርተኞች በብሔራዊ ቡድን ታቅፈው የተለያዩ ሥልጠናዎችን እየወሰዱ ራሳቸውን የሚለኩበት ሌላ ውድድር ለማካሄድም ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። ስፖርተኞቹ የውድድር ልምድ እንዲያካብቱና ዘመናዊ ከሆኑት የመወዳደሪያ መሣሪያዎች ጋር እንዲተዋወቁ የሚያደርጉ አራት የሚደርሱ ውድድሮችን ለማዘጋጀት መታቀዱንም ያብራራሉ። በአዋቂዎች እስከ 20 ስፖርተኛ የሚመረጡ ሲሆን ታዳጊዎችም ተካተውበት ለአህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ጠንካራ ዝግጅቶች የሚደረጉም ይሆናል።

በሰሞኑ ውድድር ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከመሳተፋቸው በተጨማሪ ጎረቤት ሀገር ጅቡቲም ተጋብዛ ተሳታፊ መሆን ችላለች። ውድድሩ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ በሶስት አይነት የቴኳንዶ ፍልሚያዎች ነው የተካሄደው።

ፌዴሬሽኑ ቀደም ብሎ ለቡድኖች የውድድር ይዘት ኖሮት እንዲካሄድ ሥልጠና መሠጠቱን የገለፁት አቶ ፍቅሩ፣ ከዚህ ቀደም በውድድሩ ጥቂት ክልሎች ብቻ የሚፎካከሩ ቢሆንም ዘንድሮ ግን ሁሉም ክልሎች በቂ ዝግጅት በማድረጋቸው ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ውድድር እንደነበር ተናግረዋል። ከውድድሩ ዝግጅት እስከ ፍጻሜ ድረስ የደቡብ ኮርያ ኤምባሲ በገንዘብ፣ የኩኪዮን ወርልድ ቴኳንዶ በኢትዮጵያ ደግሞ በሥልጠናና ቁሳቁስ ድጋፍ አድርገዋል።

የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ